# ኅብረተሰብ ሳይንስ

# 6ኛ ክፍል

# የመምህር መምሪያ


አዘጋጅ:-

ወንድማገኝ ገብረሕይወት

አርታኢ:-

ብርሃኑ ለሜሶ

ገምጋሚዎች:-

ዘላለም አሳጋው

ዘሪሁን ጌታቸው

ይታገሱ አጥናፉ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
Printing and Publishing LLC

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ሕትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ በትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማኅበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትብ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማኅበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት ዓለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች እነዚህ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል:: ለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2003 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-085-8

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የሕትመት መብቶች ተከብረዋል::
የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሣሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ ዓመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የሥዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ሕትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# መቅድም

ትምህርት እና ልማት እጅግ የተቆራኙና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ትምህርት በኢትዮጵያ ልማት ውሰጥ ዋንኛውና ቁልፍ መሣሪያ ነው ተብሎ የሚነገረው፡፡ በዚህ ፈጣን ዓለም አቀፋዊነት በሚታይባት ዓለማችን ውስጥ ለመኖር አዲስ እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከቶች እና እሴቶችን እያንዳንዱ ሰው ማዳበር ይጠበቅበታል፡፡ እንግዲህ በዚህ ዓላማ መሠረት ነው የአንድ ሀገር የትምህርት ሂደት ነፀብራቅ የሆነው ሥርዓተ ትምህርት ለለውጥ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ መቀረፅ ያለበት፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ አዘጋጅታ መተግበር ከጀመረች ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ ሆኗታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ተደራሽ፣ ፍትሃዊ እና ተገቢነት ያለው እመርታ በትምህርቱ መስክ አስመዝግባለች፡፡ የትምህርትንም ጥራት ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ የቆየች ሲሆን ጥረቱ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡

ይህን ሂደት ለመቀጠልም የትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል፡፡ ማዕቀፉም ሁሉንም  የትምህርት ደረጃ፤ የአፀደ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፣አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እና የመሰናዶ ክፍሎች ትምህርቶችን ያጠቃልላል፡፡ የማዕቀፉም ዓላማዎች  የሚያተኩሩት በትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲዎች ላይ ያሉትን መሠረታዊ ሀሳቦችና መርሆዎች ለማጠናከር፤ እንዲሁም ወደፊት ለሚዘጋጁት፣ የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት፣ ለዚህ የመምህር መምሪያና ለተማሪ መጽሐፍት አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴንና የመማር ብቃት አቀራረብን ያቀፉ ሆነው እንዲዘጋጁ ማስቻል ነው፡፡

አዲስ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንዲሁም፣ የተከለሱና የተሻሻሉ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሐፍት ማዘጋጀት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በየትኛውም ሀገር ቢሆን ብቸኛ መፍትሔ አይደሉም፡፡ ነገር ግን ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል፡፡ የመምህራን ሚናም ከገለጻ ሰጭነት  እስከ አነቃቂነት፣ መሪነት እና አመቻችነት ዘላቂ እንዲሆን  ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማገዝ በማዕቀፉ ላይ እና በመምህር መምሪያው ላይ የተቀመጡትን ማስተማሪያ ዘዴዎች በተመለከተ መምህራን ሥልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ወደፊትም ሥልጠናው መሰጠቱ ይቀጥላል፡፡

መምህራን ይህን መምሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡ እና የተቀመጡትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በመተግበር ተማሪዎቻቸውን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተማሪ መጽሐፍ በየምዕራፉ መጨረሻ ለተቀመጡት የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በመምህር በመምሪያ ውስጥ የተቀመጡ ቢሆንም፣ ይህ ተማሪዎችን አማራጭ መልሶችን ከመፈለግ ሊያግዳቸው አይገባም፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት መጽሐፋቸውን አንብበው አማራጭ መልሶችን እንዲያገኙ ማስቻልም ይጠበቃል፡፡

# ማውጫ


ገፅ

*መግቢያ* ..................................................................................... i

**ምዕራፍ አንድ፡- የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ፣ ሕዝቦችና አሠፋፈራቸው**

**1.1** የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮችና አንፃራዊ መገኛ ..................................1

**1.2** የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች ..........................................................5

**1.3** በመካነ ቅርስ አጠባበቅና እንክብካቤ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ......................................................................................7

**1.4** የሕዝብ አሠፋፈርና አኗኗር በምሥራቅ አፍሪካ............................10

**1.5** በሕዝብ አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች .........................................................................................15

**የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች** ............................................19

**ምዕራፍ ሁለት:- የምንኖርባት መሬት**

**2.1** የመሬት ገጽታ ........................................................................20

**2.2** የምሥራቅ አፍሪካ ዋና ዋናዎቹ የመልክዓ ምድር ገጽታዎች ........23

**2.3** የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ሀብት ................................................26

**2.4** የምሥራቅ አፍሪካ ውኃና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሙ .....................29

**2.5** ከባቢ አየር ..........................................................................32

**2.6** ዓለም አቀፋዊ የካርታ ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች (ውክሎች) ....34

**የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች** ...........................................38

**ምዕራፍ ሦስት፡- አካባቢያችን**

**3.1** የምሥራቅ አፍሪካ እፅዋትና የዱር እንስሳት ...............................40

**3.2** በምሥራቅ አፍሪካ የእፅዋትንና የእንስሳትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎች .......................................................................................43

**3.3** የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነትና በአካባቢው ላይ ያሳደረው ተጽእኖ .....46

**3.4** አፈርና የውኃ ሀብትን የመጠበቅና የመንከባከብ ዘዴዎች ..............48

**3.5** የኢትዮጵያና የምሥራቅ አፍሪካ ብሔራዊ ፓርኮችና ጠቀሜታቸው ..............51

**የምዕራፍ ሦስት የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች** ..............54


## ምዕራፍ አራት፡- ሕዝባዊ ጉዳዮች

**4.1** የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ..............55

**4.2** ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ..............58

**4.3** የሕጻናት መብቶችና አያያዝ ..............61

**4.4** የሕጻናት መብቶችን ማስከበሪያ ስልቶች ..............63

**4.5** ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባራትና መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ..............66

**4.6** የአጋርነት ጉዳዮች ..............69

**የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች** ..............72

**ዋቢ መጻሕፍት** ..............**73**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት** ..............**74**

**መርሃ ትምህርት** .............. **78**

# መግቢያ

የመምህር መምሪያ የትምህርት ርዕሶችንና ከእነዚሁ ጋር ተጎዳኝተው የሚሄዱትን የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶችን፣ የክፍለ ጊዜ ሥርጭትን፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችንና የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ያካተተ በመሆኑ ለመምህር በጣም ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ መምህር ከተመደበው ጊዜ ጋር አገናዝቦ ለሚያዘጋጀው የትምህርት እቅድ ተሟልቶ የቀረበ የጽሑፍ ማስረጃ ነው ማለትም ይቻላል፡፡

ስለዚህ የ6ኛ ክፍል የኅብረተሰብ ሳይንስ መምህር መምሪያ አራት ምዕራፎችን ያካትታል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ በንዑሳን ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ ለማስተማሩ ሥራ ምቹ የሆኑ የትምህርት ርዕሶች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ የትምህርቱ አጭር መግለጫዎች፣ ለትምህርቱ አቀራረብ የሚጠቅሙ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ የትምህርቱ ቅድመ ዝግጅቶች አቀራረብና የምዘና ስልቶች ያጠቃለለ ነው፡፡ ከእነዚህ ዝርዝር መረጃዎች አኳያ የትምህርቱ አሰጣጥ ተማሪ ተኮር ስለመሆኑ መምህራን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ስለዚህ የእርስዎ ዋነኛ ተግባር ለተማሪዎች መመሪያ መስጠት፣ አሠራሩን ማሳየትና ያላሰለሰ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ በሌለ አገላለጽ የተማሪው ተግባር "እየሠሩ መማር" ከሚለው መርህ አንፃር በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡ የምዘና ስልቶችም እየሠሩ መማር የሚለውን መርህ ከሚያካትቱት አሳታፊ ዘዴዎች ጋር የተገናዘቡ ናቸው፡፡

መምህር በማስተማር ሥራ ላይ ተሠማርተው እንደተገነዘቡት ሁሉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ተለዋዋጭ ናቸው፡፡ የተመረጠው የትምህርት ርዕስ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቆሙት የመማር ማስተማር ዘዴዎች በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት

ሊቀርብ ይችላል። ይሁን እንጂ የሚጠቀሙበት የመማር ማስተማር ዘዴ ወይም ዘዴዎች አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ ስልትን የማያጎለብቱ መሆናቸውን በአግባቡ መገንዘብ ይገባዎታል። የምዘና ስልቶቹም በእነዚሁ ዘዴዎች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው። አሳታፊ ዘዴዎችን ለምን እንጠቀማለን? ምክንያቱም እነዚህ ዘዴዎች በየንዑስ ርዕሱ መጨረሻ በተማሪው ላይ እንዲያመጣ የተተለመውን የባህርይ ለውጥ የሚያጎለብቱ በመሆናቸው ነው።

ከላይ ከቀረበው ዝርዝር ሃሳብ አነፃር የኅብረተሰብ ሳይንስን በመጀመሪያ ደረጃ በምን እንደምናስተምር የሚገልጹትን ጠቅላላ ዓላማዎችና አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ማወቅ ይኖርቦታል። ከዚህም በላይ በ6ኛ ክፍል ኅብረተሰብ ሳይንስን በማስተማር መገኘት ያለበትን ውጤት፣ የተከታታይ ምዘናንና በየርዕሱ ማጠቃለያ ላይ መሰጠት ያለበትን ሙከራ(ቴስት) ትርጉም መገንዘብ አለብዎት።

**የኅብረተሰብ ሳይንስ አጠቀላይ ዓላማዎች**

የኅብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛው እርከን ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች አንዱ ነው።

- የኅብረተሰብ ሳይንስ ተማሪዎች ስለአገራቸው፣ ስለአካባቢያቸው ከዚያም አልፎ ስለ ዓለም ምጣኔ ሀብት፣ ፓለቲካዊና ሕጋዊ ሥራዓቶችና ተቋማት እንዲያውቁ ያደርጋል።
- ተማሪዎች ኃላፊነት ተሰምቷቸው በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እኩልነትን፣ ፍትህን እንዲያከብሩ፣ መቻቻልንና አርበኝነትን እንዲያጎለብቱ፣ ለአገራቸው ታማኝ ሆነው የአገር ፍቅር ስሜት እንዲኖራቸው የአመለካከት ባህርይ ለውጥን ያዳብራል።
- ተማሪዎች የአፍሪካ ቀንድንና የምሥራቅ አፍሪካን ጥንታዊ መንግሥታትን፣ የተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝንና የዘመናዊነት ዕድገትን እንዲያውቁና እንዲረዱ ያደርጋል።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህር የሚያስተምሩትን ትምህርት ወደ ተማሪዎች ለማስተላለፍ ወይም ተማሪዎች በመሳተፍ እንዲማሩ የሚደረጉባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህራን የሚያቀርቡትን ትምህርት ከሚያዘጋጁበት፣ የትምህርቱን ግቦች ለመምታት ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች ወይም ክህሎት፣ የትምህርት ዓይነት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ወይም ከማንኛውም የትምህርቱን ግብ ሊያንፀባርቁ ከሚችሉ አግባብ ካላቸው ጠቃሚ ነገሮች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ዘዴዎች ለማስተማር የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ዓላማዎችንና ግቦችን፣ የትምህርት ርዕስ መረጣን፣ ግቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ የትምህርት ርዕሶችንና የተግባር ቅደም ተከተሎችን፣ የመማር ተግባር ስኬትን፣ የስኬቱ ግብ መምታትን ወይም አለመምታትን መገምገምን ያጠቃልላሉ፡፡

## የማስተማር መማር ዘዴዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች መግለጫ ሠንጠረዥ

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ጥያቄና መልስ (Question & Answer) | - የሚከተሉትን የሚያጠቃልሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ጥያቄዎች ለመጠቀም ይረዳል፡፡ እነሱም፡-<br>• ጠቅላላ ጥያቄዎች(general questions)<br>• ከተለያዩ አማራጭ መልሶች አሰጣጥ ጋር የተጎዳኙ ጥያቄዎች(Divergent questions)<br>• ከማነፃጸር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች(Probing questions)<br>• ከምክንያታዊነት ጋር የተገናዘቡ ጥያቄዎች<br>- ጥያቄዎቹ ትምህርት ከመጀመሩ በፊትና ትምህርቱ ቀርቦ ከተገባደደ በኋላ በአግባቡ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ | - መምህራን ከበቂ በላይ በጥያቄዎች መጠቀም መቻላቸው<br>- በእውቀት፣ በግንዛቤና በመሳሰሉት ላይ የሚመሠረቱት ጥያቄዎች ውስን አለመሆናቸው<br>- ጥያቄዎቹን መመለስ የሚያቅታቸው ተማሪዎች ቅር መሰኘት ወይም መሽማቀቅ |
| ገለጻ (explanation) | - የትምህርት ርዕሱን የሚገልጹ በቂ ቃላት መጠቀም ያስችላል፡፡<br>- ተማሪዎች ትኩረት በተሰጠው የትምህርት ርዕስ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ | - ሁልጊዜ ተማሪዎች ከመምህር መረጃ እንዲጠብቁ ማድረጉ<br>- ተማሪዎች በአብዛኛው አዳማጮች እንዲሆኑ ማድረጉ፡፡ |
| ውይይት (discussion) | - የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡<br>- እያንዳንዱ ተማሪ በንቃት እንዲሳተፍ እድል ይሰጣል<br>- ተማሪዎች የማገናዘብና ምክንያታዊ የመሆን አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡<br>- ማስተማር የሁለትዮሽ ግንኙት መሆኑን ያረጋግጣል | - ደካማ ተማሪዎች ላይ ትኩረት አለማድረጉ<br>- በጣም ጥቂት ፈጣን ተማሪዎች ውይይቱን መቆጣጠራቸው<br>- ደከም ያሉት ተማሪዎች |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| | | በመምህር ካልተጎተጎቱ በስተቀር መዳከማቸውና መፍዘዛቸው |
| ምልከታ (demonstration) | - የሚቀርበው ትምህርት ተጨባጭ እንዲሆን ይረዳል<br>- የተመረጠና ለእይታ የሚበቃ መረጃ ላይ በመመሥረት የትምህርቱን ርዕስ በቀላሉ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ | - የትምህርቱ ርዕስ የሚያጠቃልላቸውን በሙሉ አለማካተቱ<br>- ተማሪዎች ለእይታ በቀረበው ማቴሪያል ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረጉ |
| እውነትን ፈልጎ የማግኘት የማስተማር ዘዴ (Inquiry teaching learning method) | - በመማር ማስተማሩ ወስጥ ተዋናይ የሆኑትን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ ያደርጋል<br>- እንደሳይንሳዊ ዘዴ ግትር ባይሆንም በስልት መልስ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ዘዴ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለጥያቄዎች ወዲያውኑ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሌሎች ጥያቄዎች በማንሳት የበለጠ እንዲመራመሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ወድያውኑ እውነት ነው ብለው ከሚያረጋግጡ ይልቅ እውነትን ፈልገው ማግኘቱ ላይ እንዲያተኩሩ መንገድ ይከፍታል፡፡<br>- ተማሪዎችን ችግርን ለመፍታት የተለያዩና በርካታ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡<br>- ተማሪዎች ከፍተኛ የውስጥ መነሳሳት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ትምህርትን እየተደሰቱና እየጓጉ እነዲቀስሙ በር ይከፈታል፡፡ | - ተማሪዎችን ከእውነታው ጋር ለማገናኘት ያለው ብቃት አዝጋሚ መሆኑ<br>- በተወሰነ ጊዜ ሊሸፈን የተያዘ የትምህርት ርዕስ እንዳያሸፈን ማጓተቱ<br>- ዘዴው ለየት ያለ እውቀት መጠየቁ፣ ይኸውም የመመራመር፣ የመተንተን፣ የማጠቃለልና የመዘገብ ክህሎት እንዲኖር መፈለጉ |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ (Discovery teaching method) | - ከፍተኛ የተማሪዎች ተሳትፎ ይታይበታል<br>- ሰፊ ጽንሰ ሃሳቦችንና መርሆችን ለመገንዘብ ከማበረታታቱም በላይ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አብሮ የመሥራት ችሎታን ያጎለብታል፡፡<br>- ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ የመምህሩን ድጋፍ የሚፈልግ ሲሆን ተማሪዎች አበሮ የመሥራትና ችግር የመፍታት ዘዴን እንዲለማመዱ ያደርጋል | - ሰፊ የትምህርት ርዕስ ለመሸፈን ያለው ብቃት ደካማ መሆኑ<br>- የመወዳደር ስሜትን ስለሚቀንስ ተማሪዎች ፍዝ እነዲሆኑ ማድረጉ<br>- አብሮ ከመሥራት ባሻገር በተማሪዎች መካከል የውድድር ወይም የመፎካከር ስሜት አለመፍጠሩ |
| የቡድን ኘሮጀክት ዘዴ(የመተባበርና የመፎካከር የማስተማር ዘዴ) (Group project method) | - ለቡድን ሥራ መነሳሳትንና መሳተፍን ያበረታታል ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቻል<br>- በተማሪዎች መካከል የመደጋገፍ መንፈስን ያጠናክራል<br>- ተማሪዎች የሥራቸውን የመጨረሻ ውጤት ለማወቅ የበለጠ ጥረት እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡ | - ጊዜ መፍጀቱ<br>- የገንዘብ ወጪ መጠየቁ<br>- እጅግ አስተማማኝ የክፍል አመራር ከሌለ በርካታ የሥነ ምግባር ጉድለት መፍጠሩ |

## ተከታታይ ምዝናና መኩራ

### ተከታታይ ምዘና

ተከታታይ ምዘና ስለተማሪዎች እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ከተለያዩና ከበርካታ ምንጮች መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የሚከናወነው ተማሪዎች የሚያውቁትን፣ በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን ጥልቅ ግንዛቤና ከቀሰሙት እውቀት አንፃር ሊተገበሩ የሚችሉትን ለማወቅና ለማጎልበት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና ግቡን የሚመታው የተከታታይ ምዘናው ውጤቶች የትምህርቱን ሂደት ማሻሻል

ሲያስችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች የመማር ሂደት አካል ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ስለተማሪዎች የትምህርት ክትትል መረጃ ይሰጣል
- የማስተማር መማሩን ሂደት ለማሻሻልና ለማረጋገጥ ይችሉ ዘንድ መረጃዎችን በመተንተን ላይ እንድታተኩሩ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ግቦች ማሳካታቸውን መረጃ ይሰጣል፡፡
- ትምህርታዊና ተቋማዊ መሻሻል እንዲደረግ ፍንጭ ይሰጣል
- የተደረጉት ለውጦች በተማሪዎች የመማር አቅም ላይ ያመጡትን መሻሻል መገምገም ያስችላል፤

በአጠቃላይ የመማር ሂደት የተማሪ ተኮር ሥነ ዘዴ የመጨረሻ ትኩረትና ግብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታታይ ምዘና ተማሪ ተኮር የትምህርት ሥነ ዘዴ እንዲዳብር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሲከታተሉ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ማተኮር አለብዎት፡-

- ተማሪዎች ምን ተምረዋል፣ ከተማሩት ውስጥ ምን ያህል አውቀዋል? ምን ክህሎትን አዳብረዋል? ምንስ ያህል የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ለውጥ አምጥተዋል?
- አስተምሬ ለመድረስ ያስብኩበትን ግብ ከመምታት አኳያ ምን ያህል ተሳክቶልኛል?

በርካታ ዓይነት ተከታታይ ምዘናዎች ቢኖሩም አሁን የምናተኩረው በተማሪ ተከታታይ ምዘና ላይ ነው፡፡ የተማሪ ተከታታይ ምዘና የሚከተሉትን ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- ተማሪዎች ምን ያህል እውቀት እንደቀሰሙ፡፡
- የተማሪዎች ክህሎት ምን ያህል መሻሻሉንና መጎልበቱን፡፡

- ተማሪዎች ሥራ ለመሥራት ስላላቸው አቅምና በአቅማቸው ምን ያህል መጠቀም እንደሚችሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለሥራ ትጋታቸው ያላቸው ስሜት ወይም ተነሳሽነት ወይም በአጠቃላይ ስላሳዩት የአመለካከት ለውጥ፡፡

**የተከታታይ ምዘና ተግባራት ምን ምን ናቸው?**

- ለተማሪዎች ምን ያህል መማር እንዳለባቸው ማሳወቅ
- ተማሪዎች ምን ያህል ጠንክሮ በመሥራት ላይ ስለመሆናቸው ማስገንዘብ
- በትምህርቱ ምዕራፍ መገባደጃ ላይ ተማሪዎች ጠንክረው ስለመሥራታቸው ማመልከት
- የተማሪዎች ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ የደረሰበትን ደረጃ መጠቆም

**እርስዎ የትምህርቱን ሂደት እንዴት መከታተል ይችላሉ?**

- ዕለት በዕለት በሚያደርጉት ምልከታ
- ተከታታይና ዱብዳ ሙከራዎች(ቴስቶች) በመስጠት
- የፕሮጀክት ሥራና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሠሩ በማድረግና ያገኙትን ውጤት በመገምገም

**በተከታታይ ምዘና እነማን መሳተፍ አለባቸው?**

- መምህራን
- ተማሪዎች
- ወላጆች
- የትምህርት ባለሙያዎች

**ሙከራ/ፈተና**

ከትምህርት አንፃር ሙከራ ሥርዓት ባለው መንገድ የአንድን ሰው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከትና ሌሎች ተጓዳኝ የባህርይ ለውጦችን የመለካት ሂደት ማለት ነው፡፡ በርካታ የሙከራ ዓይነቶች አሉ፡፡

መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ችሎታ ለመቃኘት ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም በላይ ተማሪዎች አንዱን የትምህርት ርዕስ ምን ያህል በብቃት ተምረው መገንዘባቸውን ለማወቅ ሙከራዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**ደረጃቸውን የጠበቁ ሙከራዎች/ፈተናዎች**

አብዛኞቹ በጽሑፍ የሚቀርቡና ተማሪዎች የሚወስዷቸው ሙከራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ሙከራ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ተከልሶና በድጋሚ ጥቅም ላይ ውሎ ተመሳሳይ ውጤት ሲያስመዘግብ እንዲሁም የወሰዱት ተማሪዎች ተመሳሳይ አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ ሙከራው ደረጃውን የጠበቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአንድ ሙከራ ጥራት በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይወሰናል፡፡ እነሱም፡-

- ሙከራው የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ(Validity)
- ተአማኒነቱ(reliability)
- ተፈጻሚነቱ(practicality) ናቸው

**የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ፡-** አንድ ሙከራ ሊለካው የተገመተውን ግብ መለካት ሲችል

**ተአማኒነት፡-** በሙከራው ላይ የተገኘው ተከታታይ ውጤት ተመጣጣኝ ሲሆን ተአማኒነትን ለማረጋገጥ አንድ ሙከራ ለአንድ ቡድን በተደጋጋሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተሰጠበት ጊዜ ሁሉ በጣም የተቀራረቡ ውጤቶች ሊመዘገቡ ከቻሉ ሙከራው በጣም ተአማኒ ወይም አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ተፈጻሚነት፡-** ሙከራው የሚጠይቀው ወጪ ከአቅም ጋር መገናዘብንና የሚሰጥበት አካባቢን ምቹነት ይመለከታል፡፡ በአንፃሩ ሙከራው ከፍተኛ ወጪና ትጋት የማይጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚነቱ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሙከራውን ለማዘጋጀት ብዙ ወጪና ትጋት የሚጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚመዘገበው ውጤትም

ለመተንተን አስቸጋሪ ከሆነ የሙከራው ተፈጻሚነት አስተማማኝ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡

**የሙከራ ዓይነቶች**

አብዛኞቹ ሙከራዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባህሪያት እንዲለኩ ተደርገው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ባህሪያት የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

- የመማር ችሎታ
- የትምህርት ውጤት
- ዝንባሌና ፍላጎት

**በመማር ሂደት ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች፡-** በአቅም ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች ሲሆኑ አንድ ተማሪ የማወቅ ብቃቱን ተጠቅሞ ወደፊት ምን ያህል መሥራት እንደሚችል የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሙከራዎች አንዳንድ ጊዜ የብስለት ሙከራዎች፣ የአእምሮ ችሎታ ሙከራዎች፣ የአከዳሚክ ዝንባሌ ሙከራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

**የመማር ብቃት ሙከራ፡-** ይህ ዓይነቱ ሙከራ ደረጃቸውን በጠበቁ ተግባራት ወይም ጥያቄዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተማሪው በሕይወት ዘመኑ በመደበኛ ትምህርት ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያገኘውን እውቀትና ክህሎት እንዲያሳይ ይረዳል፡፡

**ውጤት ላይ ያተኮረ ሙከራ፡-** አንድ ተማሪ ካለው ጠቅላላ እውቀት ይልቅ አንድ የትምህርት ርዕስ በክፍል ውስጥ ተምሮ ምን ያህል እውቀት እንዳገኘ ይለካል፡፡ ከሌላው የሙከራ ዓይነት በበለጠ ትምህርት ቤቶች ውጤት ላይ ባተኮረ ሙከራ ይጠቀማሉ፡፡

አብዛኞቹ በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ወይም በኮሌጅ የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ክትትል ለማወቅ ውጤት ላይ ያተኮሩ ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡

# የእለት ትምህርት እቅድ ናሙና

የትምህርት ቤት ስም ______________________ ቀን ______________

የመምህር ስም ______________________

የትምህርት ዓይነት ______________________ ክፍል 6ኛ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 45 ደቂቃዎች

ምዕራፍ 1 ንዑስ ክፍል 6ሀ-ለ-ሐ የክፍለ ጊዜ ብዛት 1

## የትምህርቱ ርዕስ፡- የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ

ከእለቱ ትምህርት የሚጠበቅ የብቃት ውጤት

ተማሪዎች ይህን ክፍለጊዜ ካጠናቀቁ በኋላ

- የአፍሪካ ቀንድን አንፃራዊ መገኛ ይገልጻሉ

| ቀን | የሚወስደው ጊዜ | የትምህርቱ ዝርዝር ይዘት | የመምህር ተግባር | የተማሪ ተግባር | የማስተማሪያ መሣሪያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| ሰ ኞ | 5 ደቂቃዎች | ***መግቢያ***<br>*የአፍሪካ አንፃራዊ መገኛ* | *ካርታን በመጠቀም የአፍሪካ መገኛን፣ አንፃራዊ መገኛን፣ በጥያቄና መልስ ያስተዋውቃሉ፡፡* | *ካርታን በመለኮት መልሶችን ይሰጣሉ* | *የአፍሪካ ካርታ* |
| | 17 ደቂቃዎች | ***የትምህርት አቀራረብ***<br>*የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ አዋሳኝ ሀገሮች፣ ውቅያኖስ በካርታ* | *ካርታን በመጠቀም*<br>• *ምሥራቅ አፍሪካ መገኛ፣ አዋሳኝ አገሮችን፣ ባህሮችን ተማሪዎች እነዲያመለክቱ መጠየቅ* | *ካርታን ተጠቅመው የምሥራቅ አፍሪካ መገኛን ያስመለክታሉ፣ አዋሳኝ አገሮችን ይጠራሉ* | |

| ቀን | የሚወስደው ጊዜ | የትምህርቱ ዝርዝር ይዘት | የመምህር ተግባር | የተማሪ ተግባር | የማስተማሪያ መሣሪያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | 13 ደቂቃዎች | **ማጠናከሪያና ማጠቃለያ** | • ስለምሥራቅ አፍሪካ መገኛ አዋሳኝ አገሮችና ባህሮች(ውቅያኖስ) ይገልጻሉ | ስለ ምሥራቅ አፍሪካ መገኛ አዋሳኝ አገሮችን ስሞች ይጽፋሉ፣ በካርታ ያሳያሉ። | |
| | 10 ደቂቃዎች | **ክትትልና ግምገማ** | በንዑስ ርዕስ 1.1 ሥር የተቀመጡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲሠሩ ያደርጋሉ | የተሰጣቸውን የክፍል ሥራ በቡድንና በተናጠል ይሠራሉ። | |

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# ትምህርት ሚኒስቴር

# ህብረተሰብ ሣይንስ በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ
# 6ኛ ክፍል

## የህብረተሰብ ሣይንስ የ6ኛ ክፍል አጥጋቢ የመማር ብቃት

| | 6ኛ ክፍል |
|---|---|
| ህዝብ | • የምሥራቅ አፍሪካን መገኛ መለየት፤ |
| | • የምሥራቅ አፍሪካን ጥንታዊ ሥልጣኔን፣ቅርስ እና ባህል መግለፅ፤ |
| | • የምሥራቅ አፍሪካን ጥንታዊ ሥልጣኔ፣ቅርስ እና ባህል ማሳየት፤ |
| | • በምስራቅ አፍሪካ ለህዝቦች አሰፋፈር፤ አኗኗር እና ሥርጭት ልዩነት ምክንያት የሆኑ እንደ መሬት ገፅታ፣ የተፈጥሮ ሃብትና የአየር ንብረት ወዘተ መለየት፤ |
| | • ልዩ ልዩ ምልክቶችንና ቀለማትን በመጠቀም የካርታ ንድፍ ማዘጋጀት፤ |
| መሬት | • አህጉራትንና መለያ ባህሪያቸውን መለየት፤<br>• ካርታን በመጠቀም በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ዋና ዋና የመሬት ገፅታዎችን ማሳየት፤<br>• በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ልዩ ልዩ የውሃ አካላትን መለየት፤<br>• የውቅያኖስ ውሃን ከወራጅ ውሃ ጋር ማወዳደር፤<br>• በምስራቅ አፍሪካ ውሃ ያለውን ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ መግለፅ፤<br>• የከባቢ አየር ንብርብሮችን መዘርዘር፤<br>• የታችኛውን የከባቢ አየር ቅንብሮች መግለፅ |

| | | 6ኛ ክፍል |
|---|---|---|
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ | • በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ  ዋና ዋና የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ዓነቶችን መለየት |
| | | • ከልክ በላይ የማስጋጥና ደንን የማጥፋት መንስኤ እና በስነ ምህዳር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መግለፅ |
| | | • በኢትዮጵያ እና በምስራቅ አፍሪካ ያሉ ዋና ዋና ብሄራዊ ፓርኮችን መጥቀስ ፡ |
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | | • የአየር ንብረት በኢትዮጵያ እና በምስራቅ አፍሪካ ህዝብ  ሥርጭት ላይ ያለውን ተፅዕኖ መተንተን፤ |
| | | • ፈጣን የህዝብ ዕድገት  በምስራቅ አፍሪካ የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ላይ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች መገንዘብ፤<br>• በምስራቅ አፍሪካ ያሉ ዋና ዋና የውሃ፣የአየር እና አፈር ጥበቃ መንገዶችን መለየትና ማብራራት |
| | | • በምስራቅ አፍሪካ ያሉ ዋና ዋና የውሃ፣የአየር እና አፈር ጥበቃ መንገዶችን መለየትና ማብራራት |

| | | 6ኛ ክፍል |
|---|---|---|
| ህዝባዊ ጉዳዮች | ሥነ ህዝብ ነክ ጉዳዮች | • ከቫይረሱ ጋር አብረው ከሚኖሩ ልጆች ጋር አብሮ መማርና መኖር እንደሚቻል አምኖ መቀበል፤<br>• ፈጣን የህዝብ ዕድገት ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖ መተንበይ |
| | የደህንነትና የመብት ጉዳዮች | • የህፃናት መብቶችን ስለሚጥሱ ድርጊቶችንና መከላከያ መንገዶችን በምሳሌ ማብራራት፤<br>• በህፃናት መብት ጥሰት መከላከያ መንገዶች መካከል ያሉ ልዩነት መለየት |
| | አጋርነትን የማጠናከር ፕሮግራም | • የክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች እና ትብብር መድረኮችን ሚና መገንዘብ፤ |

# የሕብረተሰብ ሣይንስ መርሃ ትምህርት
# 6ኛ ክፍል

## የስድስተኛ ክፍል ሕብረተሰብ ሣይንስ ትምህርት መማር ማስተማር ውጤቶች

1. ዕውቀትና ግንዛቤን ማዳበር
   - ስለ ምስራቅ አፍሪካ አገሮች መገኛ
   - ቅርሶቻችን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የሚያጋጥሙ ችግሮች
   - የአየር ንብረት እና የተፈጥሮ ሀብት በምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች አሰፋፈርና አኗኗር ላይ ያለው ተፅዕኖ
   - የዓለም አሕጉሮችና ውቅያኖሶች ንፅህ ውሀማ አካላት በምስራቅ አፍሪካ
   - የጨዋማና ንፁህ (Fresh) ውሃ ልዩነት
   - የከባቢ አየር ንብብሮችና የታችኛው የከባቢ አየር
   - በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ የሚገኘውን የዕፅዋትና የዱር አራዊት ሥርጭትን የሚወሰኑ ሁኔታዎች አይነት፣ አሰረጫጨትና
   - የሰው ልጅ በአካባቢ ላይ ስለሚያደርሰው ተፅዕኖ መንስኤና ውጤት
   - የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴዎችና እና የብሔራዊ ፓርኮች ጠቀሜታ
   - የሕፃናት መብቶች ጥሰትና የማስከበሪያ መንገዶች
   - አሕጉራዊና አካባቢያዊ ድርጅቶች፣ አባል ሀገሮችና የምስራቅ አፍሪካ አገሮች አገርነት አቅጣጫዎች
   - የኑቢያና አክሱም ስልጣኔ ገጽታዎች
   - የኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ አክሱም እና ምስራቅ አፍሪካ
   - ሕዝብ ተተጠጋግዮና ተበታትኖ የሰፈረጣቸው የምስራቅ አፍሪካ አካባቢዎች

2. **ክህሎትንና ችሎታን ማዳበር**
   - የተለያዩ ቀለማትንና ምልክቶችን በመጠቀም  የካርታ ንድፍ ማዘጋጀት፣
   - የከባቢ አየር ንብርብሮችን መሳልና ማቅለም፣
   - በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ደህንነትና ችግሮች ላይ መከራከር፣
   - ሳይንሳዊ ተጠየቅ ክህሎችን /ማስተዋል፣ መረጃ መስብሰብና መተነንተን ሪፖርት ማዘጋጀት ለምሳሌ በሕፃናት መብቶች ጥሰቶች፣ በሕዝብ ዕድገት፣ በድህነትና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከዕድገት አንፃር ያሳያሉ፡፡
   - ብሔራዊ ፓርኮችን ለማሳየት የኢትዮጵያ ካርታ ንድፍ መስራት፡፡

3. **አመለካከትና ዝንባሌ ማዳበር**
   - ጥንታዊ ስልጣኔ እና ታሪካዊ ቅርሶች በምስራቅ አፍሪካ
   - በአካባቢያችን የሚገኙ ቅርሶችን ከጉዳት መጠበቅ
   - ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከል
   - በፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ክበባት ውስጥ መሳተፍ
   - የኩሬ አጥርና የምንጭ መጉልበት

## ምዕራፍ 1፦ የምስራቅ አፍሪካ መገኛ፣ ሕዝቦች እና አሰፋፈርና *(19 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦*** *ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፡*

- *የምስራቅ አፍሪካ አገሮች መገኛን ይለያሉ፣*
- *የምስራቅ አፍሪካን ጥንታዊ ስልጣኔና ቅርስ ያደንቃሉ፣*
- *ታሪካዊ ቅርሶችን የመጠበቅና የመያዝ አስፈላጊነት ይገነዘባሉ፣*
- *የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት በምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች አሰፋፈርና አኗኗር ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይገነዘባሉ፡፡*

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦*<br><br>• የምስራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ ይገነዘባሉ፣<br>• የምስራቅ አፍሪካ አገሮችን ይዘረዝራሉ፡፡ | ***1.የምስራቅ አፍሪካ መገኛ፣ ሕዝቦችና አሰፋፈር***<br>1.1 ***መገኛ*** *(3 ክ/ጊዜያት)*<br>• የምስራቅ አፍሪካ አገሮችና አንፃራዊ መገኛ | • ስለ አንፃራዊ መገኛ ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልፁ ተማሪዎችን መጋበዝ፡፡ በመቀጠል ቦታዎች ከአህጉራትና ታላላቅ ውሃማ አካላት አንጻር ያላቸው አንጻራዊ መገኛ መሆኑን ማስረዳት፡፡<br>• የምስራቅ አፍሪካ ካርታን በግርድፉ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሳል ተማሪዎችን በቡድን እንዲስሉ መጠየቅ፣ በመቀጠልም በቀይ ባህርና ሕንድ ውቅያኖስ አጎራባች የሆኑ ምስራቅ አፍሪካ አገሮችን እንዲጠቁሙ እያንዳንዱን ቡድን መጠየቅ፡፡ በመጨረሻም |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| | | የክፍሉ ተማሪዎች በአንድ ላይ እየተረዳዱ ጥቁር ሰሌዳው ላይ የተሳለውን ካርታ እንዲያሚሉትና በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ማድረግ |
| • የኑቢያ ስልጣኔ ቀደምትነትና መለያ ገፅታዎቹን ከአክሱም ስልጣኔ አንፃር ይገልፃሉ፣ይዘረዝራሉ፡፡<br>• በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ዋና ዋና ጥንታዊ ስልጣኔዎችን ቅርሶችን ይለያሉ፡፡ | 1.2 **የምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች** *(4 ክ/ጊዜ,ያት)*<br>• የኑቢያና የአክሱም ጥንታዊ ስልጣኔዎች<br>• ቅርሶችን የመጠበቅና የመያዝ አስፈላጊነት<br>• ቅርሶች ምንድን ናቸው? የአክሱም ስልጣኔ መገለጫ ከሆኑ ቅርሶች ምሣሌ መጥቀስ | • የኑቢያንና የአክሱምን አንፃራዊ መገኛዎች እንዲጠቁሙ መጠየቅ፣ በመቀጠልም ስለ አክሱምና ኑቢያ ባህል ማስተዋወቅ፡፡ በመጨረሻም በመወያየት የኑቢያንና አክሱም ስልጣኔዎችን አነፃፅረው ሪፖርት እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡<br>• ስለ ቅርሶች ጠቀሜታና አስፈላጊነት የተወሰነ ገለፃ በማቅረብ በየአካባቢው ያሉ ቅርሶችን በየተራ እንዲዘረዝሩ ማድረግና በየአካባቢው ያሉ ቅርሶችን እንዲንከባከቡ ማበረታታት፡፡ |
| • በመካነ ቅርሶች ላይ የተጋረጡ ችግሮችን ይለያሉ፣<br>• በመካነ ቅርሶች አጠባበቅ የሚያጋጥሙ ችግርችን ይገልጻሉ፡፡ | 1.3 **በመካነ ቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግና የሚያጋጥሙአቸው ችግሮች** *(2 ክ/ጊዜ,ያት)*<br>• ሕዝቦችን ሳያፈናቅሉ ቅርሶችን የመጠበቅ ዘዴ<br>• የጉብኝት ባህልን ማዳበር | • ተማሪዎች በቡድን በመሆን ቅርሶች በቱሪስት መስህብነታቸው የገቢ ምንጭ መሆናቸውን እንዲያስረዱ ማድረግ፡፡ ዋና ዋና የቱሪስት መስህቦችን የተጓገሮችን ብዛት / ፍስትን/ የሚያሳይ ስታቲስቲካዊ መረጃ/ከቱሪዝም ሚኒስቴር የተገኘ ሊሆን ይችላል/ ማሳየት፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • በሌሎች አገሮች ስለሚገኝ አንድ ታዋቂ የቱሪስት መስህብ ቅርስ መተረክ፡፡ ለምሳሌ በኬንያ ብዙ ጎብኝዎች የሚራገፉባት ላሙ ስለምትባለው ደሴት የውስን ጥናት ያቅርቡ፡፡<br>• በመቀጠል ተማሪዎች በየቡድናቸው በመሆን እንደ ዝርፊያ፣ ምዝበራ፣ ውድመትና መሰባበር ወዘተ ያሉ ችግሮችን ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች እንደ አክሱም ባሉ ታሪካዊ የቅርስ ቦታዎች አካባቢ እንዴት መንቀሳቀስ እንደሚገባ በራሪ ፅሑፍ ማዘጋጀት፡፡ |
| • በምስራቅ አፍሪካ ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሰፈረባቸውን አካባቢዎች ይለያሉ፣<br>• በምስራቅ አፍሪካና ኢትዮጵያ የሕዝቦች ፍልሰትና እንቅስቃሴ መንስኤና ውጤቶችን ይገልጻሉ፣ | **1.4 .የምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች አሰፋፈርና አኗኗር**<br>*(6 ክ/ጊዜ,ዖት)*<br>• የሕዝቦች አሰፋፈር<br>• የሕዝቦች እንቅቅስቃሴ<br>• ፈጣን የሕዝብ ዕድገትና ውጤቶቹ<br>• የከተሞች መስፋፋትና በማህበረሰቡና ባህል ላይ ያለው ተፅዕኖ | • ተማሪዎች የአፍሪካ ካርታን በመጠቀም ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸውን አካባቢዎች እንዲጠቁሙ ማድረግ፣<br>• ለምሳሌ የኦሮሞ ሕዝቦች መስፋፋትን በመጥቀስ የሕዝብ እንቅስቃሴ መንስኤዎችና ውጤቶችን መወያየት፡፡<br>• የሕዝብ ዕድገትና እንቅስቃሴ /ፍልሰትን/ በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች መካከል ማነፃፀር |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በኢትዮጵያ በኬንያና እና በታንዛኒያ ደጋማ አካባቢዎች የሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ የሆነባቸውውን ምክንያቶች ይለያሉ፡፡፡<br>• በምስራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚኖረውን ተፅዕኖ ይለያሉ፡፡<br>• የከተሞች መስፋፋት ከባህልና ማህበራዊ ለውጥ አንጻር የሚያመጣውን ለውጥ ይዘረዝራሉ፡፡ | | • ተማሪዎች ቁልፍ የሕዝብ ፍልሰት ምክንያቶች ናቸው በሚሏቸው ሁኔታዎች ላይ ማወያየት፡፡ ለምሳሌ በግጦሽ መሬት ዕጥረት ምክንያት፣ የተሻለ ስራ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት<br>• **ውስን ጥናት፡**-አዲስ አበባን ከናይሮቢ ጋር ማነፃፀር /የሁለቱን ከተሞች ከገጠር ወደ ከተማ የፈለሱ ሰዎችን አኗኗር የሚተነትን ውስን ጥናት ማቅረብ፡፡<br>• የከተሞች መስፋፋት በኀብረተሰቡና ባህል ላይ ያለው ተጽእኖ ተማሪዎች ውይይት ያድርጉ<br>• ከመኖሪያ ቤት ርቆ መኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች እንዲወያዩ ማድረግ |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| • በሕዝቦች አሰፋፈርና አኗኗር መለያየት አስተዋፅኦ ያላቸው ሁኔታዎችን ይተነትናሉ፡፡<br>• የፖለቲካ አለመረጋጋትና የርስ በርስ ጦርነት /ግጭት/ በሕዝብ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይተነትናሉ፡፡ | 1.5 **በሕዝቦች አሰፋፈርና አኗኗር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች** *(4 ክ/ ጊዜያት)*<br>• የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት<br>• ፖለቲካዊ አለመረጋጋትና የርስ በርስ ግጭት | • በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች እና በኬንያ ጠረፋማ ዝቅተኛ ቦታዎች የተፈጥሮ ሀብቱን ለምሳሌ የአፈር ሁኔታ፣ ውሀ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመውሰድ ስለ አሰፋፈሩ ሁኔታ ውስን ጥናት እንዲያጠኑ ማድረግ፡፡<br>• የየአገሮቹን ወሰን የሚያሳይ የምስራቅ አፍሪካ ካርታን ጥቁር ሰሌዳው ላይ መሳል፡፡ ከዚያም የርስ በርስ ግጭቶችና አለመረጋጋት የሚታዩባቸውን አካባቢዎች ያውቁ እንደሆነ ለተማሪዎች ጥያቄ ማንሳት፡፡ የተማሪዎቹንም ምላሾች ሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡<br>• በመጨረሻም ሁለት በግጭትና አለመረጋጋት ምክንያት የሕዝብ ፍልሰት የተከሰተባቸውን ቦታዎች የሚያስረዳ ንፅፅራዊ ጥናት ማቅረብ፡፡ ለምሳሌ ቦታዎቹ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ፣ ኡጋንዳ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ |

## ግምገማና ምዘና

መምህሩ/ሯ እያስተማረ/ች ያለውን ትምህርት እስኪያጠናቅቅ/እስክታጠናቅቅ ድረስ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ሂደት በተከታታይ ይገመግማሉ፡፡ የግምገማ ውጤቱንም ከተቀመጠው ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ አንፃር በማየት ተማሪው የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ ማሟላት አለማሟላቱን ይወስናል፡፡ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ የሚያሟሉ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ፡-

- የምስራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ ይለያሉ፣
- የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮችን ይዘረዝራሉ፣
- የኑቢያንና አክሱምን ስልጣኔዎች አነሳሶችና ገጽታዎችን ይለያሉ፣
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና ታሪካዊ የጥንት ስልጣኔ የውርስ ቦታዎችን ይገልፃሉ፡፡
- ቅርሶችን በተመለከተ የሚታዩና የማይታዩ ችግሮችን ይተነትናሉ፡፡
- የተሻሉ የቅርስ አጠባበቅ ዘዴዎችን ይፅፋሉ፡፡
- ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሰፈረባቸውን የምስራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ይለያሉ፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ እንቅስቃሴና ፍልሰት መንስኤና ውጤቶችን ይገልፃሉ፣
- በኢትዮጵያ ከፍተኛ /ተራራማ/ አካባቢዎች ሕዝብ እንዲሰፍር የሚያደርጉ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችን ይለያሉ፣
- በአሰፋፈርና አኗኗር ይተገበራል ላይ ልዩነት በሚያስከትሉ ምክንያቶች ላይ የወያያሉ፣

ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በላይ የሚያመጡ ተማሪዎች ይበረታታሉ፡፡ ውጤታቸውም ለበለጠ ስራ እንዲያበቃቸው ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በታች የሚያመጡ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍና ርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የተለየ ትኩረት ሊደግላቸው፣ በእረፍት ሰዓትና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪም ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የምንኖርባት መሬት (19 ክፍለ ጊዜያት)

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፡

- የዓለም አህጉራትን እና ውሀማ አካላትን ይለያሉ፣ ንፁህ እና ጨዋማ ውሃን ያነፃፃራሉ፣
- የምስራቅ አፍሪካ መልከአምድራዊ አቀማመጥን /ገፀ - መሬትን/ ያብራራሉ
- የከባቢ አየር ንብርብሮችን ይለያሉ፣ የታችኛው የከባቢ አየር ክፍል ይዘቶችንም ይገልፃሉ፣
- የምስራቅ አፍሪካን ተፈጥሮአዊ አካባቢ ለማሳየት የተለያዩ ቀለማትንና ምልክቶችን በመጠቀም የአፍሪካን ካርታ ያዘጋጃሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-<br><br>• አህጉራት ይዘረዝራሉ፡፡<br>• የዓለም ዋና ዋና ውቅያኖሶችን ይጠራሉ፡፡<br>• የውሃ አካላት አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡<br>• የምሥራቅ አፍሪካ የውሃ አካሎችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ይገነዘባሉ፡፡ | 2. ***የምንኖርባት መሬት***<br>2.1. **የመሬት ገጽታ***(4 ክ/ጊዜያት*<br>• አህጉራት<br>• ውሀማ አካላት<br>▪ የውሃ አይነቶች (ጨዋማና ጨዋማ ያልሆኑ ውሀማ አካላት)<br>▪ የምስራቅ አፍሪካ ውሀማ አካላትና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች | • የዓለም ካርታ በመጠቀም ሰባቱን አሕጉራት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ማለትም ኤስያ፣ አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አንተርክቲካ፣ ከአውስትራሊያና አውሮፖ እያሉ እንዲናገሩ መጠየቅ በመቀጠል፤<br>• ዋና ዋና ውሃማ አካላትን እንዲጠቅሱ መርዳት፡፡<br>• ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ ውቅያኖስ ባሕሮች፣ ሀይቆች እና ወንዞች በማለት እንዲመልሱ ማድረግ ፤ ይህም ማለት፡-<br>ውቂያኖሶች - ህንድ፣ ፓስፊክ ...<br>ባህሮች - ሜድትራኒያንና ቀይ ባህር |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ሀይቆች - ቪክቶሪያ ጣና<br>ወንዞች - አባይ፣ አማዞን፣ ኮንጎና ሚሲሲፒ<br><br>• በመቀጠል ተማሪዎች ምሳሌ በመስጠት ጨዋማና ጨዋማ ያልሆነ እያሉ የውሃማ አካላት አይነቶችን እንዲለዩ ማድረግ፣<br>• ከዚያም ተማሪዎች ስለ ውሀማ አካላት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለምሳሌ መጓጓዣ፣ መስኖ፣ ዓሳ ርባታ፣ እና የሃይል ማመንጫ ወዘተ እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎች ስለ አሕጉራት፣ የምስራቅ አፍሪካ ተፈጥሮአዊ አካባቢዎች፣ ውሃማ አካላትና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ማጠቃለያ እንዲሰጡ ማበረታታት፣<br>• የናይል ወንዝን በተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ፣<br>• ተማሪዎች የዓለም ካርታ በማዘጋጀት መማሪያ ክፍላቸው ግድግዳ ላይ መስቀል፣ በተጨማሪም በደብተሮቻቸው ላይ የዓለምን ካርታ እንዲስሉ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የምሥራቅ አፍሪካን ዋና ዋና መልካአምድራዊ አካባቢዎች ይለያሉ፡፡<br>• የታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆን ጠቀሜታ ይገልጻሉ፡፡ | **2.2. የምስራቅ አፍሪካ ዋና ዋና የመልክአ ምድር ገጽታዎች** *(4 ክ/ ጊዜያት)*<br>• የምስራቅ አፍሪካ መልካአምድራዊ ገጽታዎች<br>• ታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ | • ተማሪዎች በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ በተንጠለጠለው ካርታ ላይ የሚያውቋቸውን የምድር ገፅታዎች እንዲያመለክቱ ማድረግ፡፡ መምህሩ/ሯ/ ተጨማሪ ገለፃ መስጠት፡፡ ለምሳሌ ስምጥ ሸለቆ፣ እንደ ሌኒንጋጊ፣ ኪሊማንጃሮ ተራራ፣ የኬንያ ተራራ፣ የራስ ዳሽን ተራራ የኮባር ስምጥ /ዳሎል/ ያሉ ቅልጤ አለት ተራራዎች፡፡<br>• ተማሪዎች ቅልጤ አለት ተራሮች ከታላቁ የስምጥ ሸለቆ አንፃር እንዲያመለክቱ መጠየቅ፡፡ የስምጥ ሸለቆ አካባቢን ከካርታው ላይ በተለዩ ቀለም መቀባት /ማድመቅ/ አያይዞም ስምጥ ሸለቆ መቼና እንዴት እንደተፈጠረ ማብራራት፡፡ |
| • በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ወንዞችን፣ ሀይቆችንና ባህሮችን ይናገራሉ፡፡<br>• የጨዋማና ጨዋማ ያልሆኑ ውሃማ አካላትን ያነፃፅራሉ፡፡ | **2.3. የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ሀብት** *(2ክ/ጊዜያት)*<br>• የምስራቅ አፍሪካ ሀይቆች፣ ወንዞችና ባህሮች<br>• ጨዋማና ጨዋማ ያልሆነ ውሃ | • ተማሪዎች ሌሎች በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ወንዞችንና ሀይቆችን እንዲሁም ሕንድ ውቅያኖስንና ቀይ ባህርን ጨምረው ከካርታው ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ በመቀጠል ካርታው ላይ ምልክታቸውን ማስቀመጥ፣ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
| --- | --- | --- |
| | | • **ተግባራዊ ሙከራ፡-**ከዚያም ሁለት ጠርሙሶችን አንደኛው በንፁህ ውሀ የተሞላ ሌላው ጨዋማ በሆነ ውሀ የተሞላ ተመሳሳይ ነገር /ካርቶን፣ የፓርከር ቀፎ./ ተንሣፋፊ በማስቀመጥ ተግባራዊ ምርምር ያድርጉ፡፡ በምላሳቸው ቀምሰው እንዲለዩ ማዘዝ፡፡፡ ለግብርና፣ ለአሳ እርባታ የሚውሉ የትኛው ነው? ለምን? ብሎ መጠየቅ፡፡<br>• ጨዋማ ውሃ ባልሆነው የቪክቶሪያ ሃይቅ ላይ አሣ ማስገርን በተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ<br>• ጨዋማ ውሃ በሆነው የሙት ባህር ላይ ውስን ጥናት ማቅረብ፡፡ በማያያዝም ጨዋማ ከሆኑት የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ውስጥ ለምሳሌ ናኩሩን የተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ፡፡ |
| • የምሥራቅ አፍሪካ ውሃማ አካላትን ኢኮኖሚዊ ጥቅም ይገልጻሉ፡፡<br>• የውሃን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በቁልፍ ምሣሌዎች አስድግፈው ይለያሉ፡፡ | 2.4. **የምስራቅ አፍሪካ ውሃና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ**<br>*(2 ክ/ ጊዜያት)* | • የውሀማ አካላት ጥቅሞችን በሚያስቡት መንገድ እንዲዘረዝሩት በማድረግ ይህንንም በሰሌዳው ላይ ለትራንስፖርት፣ ለመስኖ ስራ፣ ለአሳ ማስገር፣ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ በሚሉ ርዕሶች ስር ማደራጀት፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ውሃ የአንድን አካባቢ ስትራቴጂያዊ ተፈላጊነት እንደሚወሰን ይረዳሉ፡፡ | | • ከዚያም አሳ እርባታ በጅቡቲ፣ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት በኡጋንዳ፣ የመስኖ ስራ በኢትዮጵያ እንዲሁም የጭነት መርከቦች በሞምባሣ የተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ |
| • የአካባቢ አየር ጥንቅሮችን ይለያሉ፡፡<br>• የታችኛው ከባቢ አየር ጥንቅሮችን ያብራራሉ፡፡<br>• የከባቢ አየር ንብርብሮችን በመሳል በከፍታ ይለያሉ፡፡ | 2.5. **ከባቢ አየር** *(2 ክ/ ጊዜያት)*<br>• የከባቢ አየር ንብርብሮች<br>• የከባቢ አየር ታችኛው ክፍልና ጥንቅሮች | • ተማሪዎች ስለ ከባቢ አየር የሚያውቁትን እንዲገልፁ መጠየቅና ትርጉሙን በሰሌዳው ላይ ሃሣብ እንደሰጡ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም የተሻለውን ትርጉም መምረጥ፡፡<br>• የከባቢ አየር ንብርብሮችን (ሥረ ህዋን፣ ስትራሰስፌር፣ ሥሯጽ ሕዋንና ውቅ ሕዋን) የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫ በሰሌዳው ላይ በማዘጋጀት እያንዳንዱ ንብርብር ያለውን ጥልቀት በተመለከተ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• አውሮፕላኖች የሚበሩበትን ከፍታ መግለፅ፡፡ ለምሳሌ ኤሌኮፕተሮች፣ የሕዋ መንኮራኩሮች ወዘተ<br>• በማያያዝ በተለይ የታችኛው የከባቢ አየር ንብርብር ክፍል በያዛቸው ጋዞች /ናይትሮጂን፣ ኦክስጂን፣ ካርቦንዳይኦክሳይድ ሌሎች / የተሠራ መሆኑን መግለፅ |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| • ቀለማት ለካርታ አተረጓጎም ያላቸውን ሚና ያደንቃሉ፡፡<br>• ለካርታ ስራና አተረጓጎም የሚጠቅሙ ቅልመቶችን እና ምልክቶችን ይለያሉ፡፡<br>• የካርታ ቅልመቶችን ምልክቶችን/ውክሎችን/ በመጠቀም የካርታ ንድፍ ያዘጋጃሉ፡፡<br>• ቀላል የካርታ ሕዳግ መፍቻ ያዘጋጃሉ፡፡ | 2.6. **ዓለምአቀፋዊ የካርታ ምልክቶችና ውክሎች**<br>*(5 ክ/ ጊዜ,ያት)*<br>• የቀለም ጥቅም<br>• ዋና ዋና ምልክቶችና ውክሎች | • **ውስን ጥናት፦**በሚከተለው ጉዳይ ላይ ውስን ጥናት ማካሄድ፡፡ ከፍታ ሲጨምር የአየር እምቅታ እና የኦክሲጂን መጠን ይቀንሣል፡፡ስለሆነም ወደ ተራራና ሕዋ ከ10,000 ጫማ በላይ የሚወጡ ሰዎች ኦክሲጂን መያዝ አለባቸው፡፡ኦክሲጂን ለጤናማ አእምሮና አስተሳሰብ ያስፈልጋል፡፡<br><br>• ባለ 1፡50,000 መስፈርት ካርታ ማዘጋጀትና ሰሌዳ ላይ መስቀል፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱ የካርታው ቅልመት ምንን ለማመልከት እንደዋለ ይለዩ፡፡ አረንጓዴው ዕፅዋትን፣ ሰማያዊ ውሃማ አካላትን፣ ቡናማው ከፍተኛ ቦታዎችን፣ ቢጫው ዝቅተኛ አምባ ምድር፣ ነጩ የተራራ ጫፎችን፣ ቀዩ ዋና ዋና መንገዶችን በማለት ይፃፉ፡፡<br>• የካርታ መፍቻ ምንነትን መግለፅ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች አንድ ባለ 1፡50,000 በመጠቀም ቀላል የካርታ መፍቻ እንዲያዘጋጁ ማድረግ<br>• አያይዞም የካርታውን ምልክቶችና ውክሎች እንዲስሉና ስም እንዲሰጡ ማዘዝ ለምሳሌ የኢንዱስትሪ መንደር፣ ትምህርት ቤቶች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ የባቡር |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| | | ሃዲዶች፣ መንገዶች፣ የደን ቦታዎች፣ መኖሪያ ሰፈር ወዘተ…<br>• በመጨረሻም ተማሪዎች የካርታ ቅልመቶችን፣ ምልክቶችንና ውክሎችን በመጠቀም የአካባቢያቸውን ካርታ እንዲያዘጋጁ ተግባር መስጠት፡፡ |

## ምዘናና ግምገማ

መምህሩ/ሯ እያስተማረ/ች ያለውን ምእራፍ እስኪያጠናቅቁ ድረስ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ሂደት በተከታታይ ይገመግማሉ፡፡ የግምገማ ውጤቱንም ከተቀመጠው ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ አንፃር በማየት ተማሪው የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ማስተማር ውጤት ማሟላት አለማሟላቱን ይወስናሉ፡፡ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያውን የሚያሟሉ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ፡-

- ሰባቱን አህጉራትና ዋና ዋና የመልከዓምድር ዓይነቶችን መዘርዘር፣
- የዓለም ዋና ዋና ውቅያኖሶችን መለየት፣
- ጨዋማ የሆኑና ጨዋማ ያልሆነ ውሀን ልዩነት መናገር፣
- ውሀማ አካላትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ይገነዘባሉ-የከባቢ አየር ንብርብሮችን ይለያሉ፣
- የታችኛው ከባቢ አየር ጥንቅሮችን ማብራራት፣
- ዓለምአቀፋዊ የካርታ ምልክቶችና ውክሎችን መጠቀም፡፡

ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የመማር ማስተማር ውጤት በላይ የሚያመጡ ተማሪዎች ይበረታታሉ፡፡ ውጤታቸውም ለበለጠ ስራ እንዲያበቃቸው ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በታች የሚያመጡ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍና ርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የተለየ ትኩረት ሊደረግላቸው፣ በእረፍት ሰዓትና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪም ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

# ምዕራፍ 3፦ አካባቢያችን *(14 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦*** *ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፡*

- በምስራቅ አፍሪካ የዕፅዋትንና ዱር አራዊትን ዓይነቶችና አስረጫጨታቸውን የሚወስኑ ሁኔታዎችን ይለያሉ፣
- የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ጣልቃ ገብነት መንስኤና ውጤት ይገነዘባሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀምን ይገነዘባሉ፤ የብሔራዊ ፓርኮችን አስፈላጊነትም ያብራራሉ፣
- አካባቢያቸውን ከጉዳት የመከላከልና የመጠበቅ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦<br><br>• የዱር እንስሳትን ሕልውና ከእጽዋት ስርጭት ሁኔታ ጋር ያዛምዳሉ፣<br>• እንስሳት የሚኖሩበትን አካባቢ ለመልመድ ያላቸውን ሁኔታ ይገነዘባሉ፣ | **3. አካባቢያችን***(2 ክ/ጊዜያት)*<br>**3.1. የምስራቅ አፍሪካ እጽዋትና የዱር እንስሳት** *(2 ክ/ጊዜያት)*<br>• የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሣት ዓይነቶችና ስርጭት<br>• እንስሳትና ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸው ስምሙነት | • ተማሪዎች የምድር ወገብ እርጥብና ሞቃት ደኖች፣ የሳር ምድር እና የበረሃ እጽዋት አይነቶችን እንዲያብራሩ መጠየቅ፡፡ በተማሪዎች የተዘረዘሩትን እነዚህ የእፅዋት ዓይነቶችን በሰሌዳው ላይ በየርእሱ ከፋፍሎ ከጻፏ በኋላ በእያንዳንዱ ርእስ ስር ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት፡፡<br>• ከዚያም ሶስት ውስን ጥናት ከሶስት ሀገራት በመውሰድ ማነፃፀር፡፡ ለምሳሌ በረሃ በኢትዮጵያ፣ የሳር ምድር ኬኒያ /ማሳይ ማራ/ የተራራ ደን በኡጋንዳ፡፡<br>• በማያያዝም በእያንዳንዱ ምቹጌ የሚገኙ የዱር እንስሳትን በሶስት መድቦ መዘርዘር፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | አንዳንድ ዝርያዎች ከአንድ በላይ በሆነ ምቹጌ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን ማስገንዘብ |
| • የተፈጥሮ እጽዋትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎችን ይለያሉ፣<br>• በሰው ልጅ ጫና የተፈጥሮ አካባቢ ሲጎዳ የዱር እንስሳት ሕልውና እንደሚጎዳ ይገነዘባሉ፡፡<br>• በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ እጽዋትና የዱር እንስሳት ስነ ውበታዊ ዕሴትን ያደንቃሉ፣<br>• የዱር እንስሳትንና የተፈጥሮ አካባቢን መጠበቅ ለቱሪዝም ያለውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ፡፡ | **3.1.1. በምሥራቅ አፍሪካ የእጽዋትንና እንስሳትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎች** *(2 ክ/ጊዜያት)*<br>• የእጽዋትንና እንስሳትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎች (ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሁኔታዎች)<br>• የዱር እንስሳት፤ የዓለማችን ዕፅዋት ሥርጭት | • ተማሪዎች የተፈጥሮ እጽዋት ስርጭትን የሚወስኑ ሁኔታዎችን እንዲናገሩ ማድረግ<br>• በመቀጠል ስለ የዓለም የሙቀት መጠን መጨመር፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና የእርሻ ስራ ላይ መወያየት<br>• የድርቅ መከሰት በፓርኮች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ እንዲሁም በእርሻ መሬት መስፋፋት የደን መጨፍጨፍ ምክንያት የዱር እንስሳት ስደት ለምሳሌ ዝሆን፣ የሚያሳይ ውስን ጥናት ማቅረብ፡፡<br>• በመጥፋት ላይ ወይም ለመጥፋት በመቃረብ ላይ የሚገኙ የእንስሳት ዝርያዎችን መዘርዘር፤የችግሩን አሳሳቢነት መተንተን፡፡<br>• በመጨረሻም ለትርፍ ያልተቋቋመው አለም አቀፍ የዱር እንስሳት ጥበቃ ጥረት ድርጅት ምንነት መግለፅ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የሰው ልጅ ተግባሮችን ይገመግማሉ፡፡<br><br>• በተፈጥሮ እጽዋት ብክነት የሰው ልጅ ታላቅ ድርሻ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ | **3.2. የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነትና የአካባቢ ተጽእኖ**<br>*(4 ክ/ጊዜያት)*<br>• *መንስኤዎች፡- የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ የግጦሽ ሳር ፍለጋ፣ ለቤት ስራና የሀይል ምንጭ፣ በአየር ንብረት መዛባት እና በግጭት ምክንያየት የስደት መጨመር ውጤቶች፣*<br>• *ውጤቶች፡- የአፈር መከላት፣ የእፅዋት ውድመት፣ የውሃ እጥረት፣ ድርቅ፣ ርሀብና ስደት* | • *ለደን ሀብት መመናመን መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችን ለምሳሌ የሕዝብ ቁጥር እድገት፣ እየዘረዘሩ መወያየት፡፡ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች የሚታየውን የእጽዋት ውድመት እንደ ምሳሌ በማንሳት መወያየት፡፡*<br>• *በማያያዝም ለሕዝብ ቁጥር ዕድገት መንስኤ የሆኑ ሁኔታዎችን ውልደትና ፍልሰት በማለት መተንተን፣ ከዚያም በሀይል አቅርቦት እና የመጠለያ ችግር ወዘተ በማለት መተንተን፣ ከዚያም በሀይል አቅርቦት እና የመጠለያ ችግር ወዘተ በማለት ውጤቱን መግለፅ፡፡*<br>• *ተማሪዎች በየቡድናቸው በመሆን ስለ ድርቅ፣ የአፈር መከላት፣ የደን መጨፍጨፍ፤ንር ማስጋጥ የውሀ እጥረት፣ ድርቅና ርሃብ እንዲሁም የሕዝብ ፍልሰት በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት አድርገው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡*<br>• *እያንዳንዱ ቡድን የተሰጠውን የጥናት ርዕስ በተቻለ መጠን በቂ መረጃ አደራጅቶና ተንትኖ እንዲያቀርብ ማዘዝ፡፡* |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • በመቀጠልም ኢትዮጵያና ኬንያን በመውሰድ አንዱ በአፈር ለምነት መመናመን ሁለተኛው በግጦሽ መሬት መራቆት ያተኮሩ ሁለት ውስን ጥናቶችን ማቅረብ፡፡ |
| • የአፈርሀብትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይገልፃሉ፡፡<br>• የውሃ ሀብትን እንዴት መያዝና መጠቀም እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡<br>• ውሃን እንዴት ማጣራት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ | **3.3. የአፈርና ውሃ ሐብትን መጠበቅና መንከባከብ ዘዴዎች**<br>*(4 ክ/ጊዜ/ያት)*<br>• ድነና፣ መልሶ ድነና ደንን ማዝመር፤<br>• እርከን ስራ፣<br>• አግድም ማረስ፣<br>• የአዝዕርት መፈራረቅ፣<br>• ለሰው ሰራሽ ኬሚካል ማዳበሪያ ከመጠቀም ይልቅ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ፣<br>• ውሃን ማቆር/ማቀብ፣<br>• ውሀን ማጣራት፣<br>• የውሃ ብክለትን መከላከል፣<br>• የምንጭና ኩሬ ጠረጋ፣ | • ለድነና ምቹ በሆኑ የዛፍ አይነቶች ላይ ይወያዩበት፡፡<br>• ግብርና ከደን ጋር ማጣመር ለኮምፖስት ስራ አመቺ መሆኑን የተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ፤ እንዲሁም በኬንያ የአዝዕርት መፈራረቅ በተመለከተ መወያየት፡፡<br>• አግድም እርሻ የሚያሳይ ስዕል በመጠቀም መወያየት፡፡<br>• ለድነና አስፈላጊ የሆኑ ዛፎችን በተመለከተ ውይይት ማካሄድ፡፡<br>• ስለ ውሃ ማቆር/ዕቀባ/ በስዕላዊ መግለጫ በመታገዝ መወያየት፡፡<br>• በመጨረሻም ተማሪዎች ስለ ውሃ ንፅህና አጠባበቅ የምንጭና ኩሬ ጠረጋ ተወያይተው በራሪ ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የብሔራዊ ፓርኮች ዓላማና ጥቅምን ይተነትናሉ<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮችን ከካርታ ላይ ያመለክታሉ<br>• በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና የብሔራዊ ፓርኮችን ይለያሉ፡፡ | **3.4. የኢትዩጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ጠቀሜታቸው**<br>*(2 ክ/ጊዜያት)*<br>• የኢትዩጵያ ብሄራዊ ፓርኮች መገኛ፣ ጠቀሜታና ዓላማ ለአጠባበቅ፣ ለምርምርና ለጥናት ያላቸው አመቺነት<br>• በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ፓርኮች ከዱር እንስሳትና አካባቢ ጥበቃ አኳያ ያላቸው ፋይዳ | • ተማሪዎች ከአሁን በፊት የሚያውቋቸውን ፓርኮች እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ምላሻቸውን ሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡ በፓርኮቹ ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳትን መለየት፣ ከዚያም ስለ ፓርኮች ውጤታማነት መከራከር፣ በፓርኮች ላይ እንደ አዋሽ፣ የሰሜን ተራሮች፣ ነጭ ሳር፣ የባሌ ተራሮች፣ ማጎ፣ ኦሞ፣ ጋምቤላና ያንጉዲ ራሳ ያሉ መወያየት፡፡<br>• በመቀጠልም ተማሪዎች ካርታ በመጠቀም የብሔራዊ ፓርኮችን መገኛ እንዲያመለክቱ ማድረግ<br>• ውጤታማ የሆነ የኢትዮጵያ ፓርክ አስመልክቶ ውስን ጥናት አዘጋጅቶ ማቅረብ፣<br>• በኬንያ ስለ ማስቶማራ ፓርክ ውስን ጥናት ማቅረብ<br>• በመጨረሻም ምስራቅ አፍሪካን የሚያሳይ ካርታ በመጠቀም ስለ ፓርኮች ስርጭት፣ የአየር ንብረትና ዕፅዋት እንዲሁም ለሚገኙት የዱር እንስሳት ዝርያዎች መወያየት፡፡<br>• በናይሮቢ ወላጅ አልባ የዱር እንስሳት ሁኔታን በተመለከተ ውስን ጥናት ማቅረብ፡፡ |

## የምዘናና ግምገማ

መምህሩ/ሯ እያስተማረ/ች ያለውን ምእራፍ እስኪያጠናቅቁ ድረስ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ሂደት በተከታታይ ይገመግማሉ፡፡ የግምገማ ውጤቱንም ከተጠበቀው ውጤት አንፃር በማየት ተማሪው የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ ማሟላት አለማሟላቱን ይወስናሉ፡፡ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያውን የሚያሟሉ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ፡-

- የዱር እንስሳት ስርጭትን ከዕፅዋት ስርጭት ጋር ማዛመድ፣
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ስርጭትን የሚወስኑ ዋና ዋና ሁኔታዎችን መለየት ፣
- የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር አራዊት ያላቸውን ስነ ውበታዊ ፋይዳ መረዳት፣
- የሰው ልጅ በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ማጤን፣
- የአፈርና ውሃ ሐብትን እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ዘዴ መቀየስ፣
- ብሔራዊ ፓርክ ምንድነው የሚለውን ማብራራት፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮችን በካርታ ላይ ማሳየት፣
- በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ፓርኮችን ማሳየት፣
- የብሔራዊ ፓርኮችን ጠቀሜታ መተንተን
- ብሔራዊ ፓርኮችን ከጉዳት መከላከል እንደሚገባ ማመንና መቀበል፡፡

ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የመማር ማስተማር ውጤት በላይ የሚያመጡ ተማሪዎች ይበረታታሉ፡፡ ውጤታቸውም ለበለጠ ስራ እንዲያበቃቸው ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በታች የሚያመጡ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍና ርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የተለየ ትኩረት ሊደረግላቸው፣ በእረፍት ሰዓትና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪም ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ምዕራፍ 4፡- የሥነ ህዝብ ጉዳዩች *(16 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፡

- ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ይሳተፋሉ፣
- የሕፃናት መብቶች ጥሰትና መከላከያ መንገዶችን በምሳሌ ያስረዳሉ፣
- የምስራቅ አፍሪካ አጋር መንግስታትን፣ አባል ሀገሮችንና የጋራ ዓላማዎቻቸውን ይለያሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-<br>• ኤች አይ ቪ/ ኤድስን በመከላከል ረገድ የሕብረተሰብ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ፡፡<br>• ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖችና ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዴት መማርና መኖር እንደሚቻል አወንታዊ አመለካከት ያዳብራሉ፡፡<br>• ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖችን ከማግለልና ከማዳላት ይልቅ በምትኩ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳትና | **4.ህዝባዊ ጉዳዮች**<br>**4.1. የሥነ ሕዝብ ነክ ጉዳዮች**<br>(3 *ክ/ጊዜያት)*<br>• በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎና በዜግነት ሃላፊነት ስሜት ኤች አይ ቪ/ ኤድስን መከላከል<br>• ማግለልና መድሎን ማቆም<br>• ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ | • ተማሪዎች ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ፡፡ ከዚያም ቫይረሱ በደማቸው ወስጥ ያለባቸውን ወገኖችን እንዴት መንከባከብና ድጋፍ ማድረግ እንደሚቻል መወያየት፣<br>• በመቀጠልም በአብዛኛው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ወገኖችን ለመርዳት በሕብረተሰቡ የተደረገ ምናልባትም መንንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ውስን ጥናት ወይም ዘገባ ማቅረብ፡፡<br>• በኢትዩጵያና በኡጋንዳ በችግሩ የተጎዳ አንዳንድ ቤተሰብ በመውሰድ ውስን ጥናት ወይም ዘገባ ማቅረብ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| አብሮ ለመኖር ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡ | | • ተማሪዎች ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያሉ ጓደኞቻቸው ስሜት እና በጓደኞቹ የሚደረግለትን እገዛ የሚያሳይ ሚና ጨዋታ ማዘጋጀት፣<br>• የችግሩን ግዝፈትና አሳሳቢነት ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ማወያየት፡፡<br>• ችግሩን አጉልተው የሚያሳዩ መረጃዎችን በመተንተን እራሳቸው ተማሪዎች በት/ቤትና ከት/ቤት ውጭ ሊሰሯቸው የሚችሏቸውን ተግባሮች እንዲያቅዱ መጠየቅ፡፡ |
| • የሕዝብ ብዛት ዕድገት በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ከምስራቅ አፍሪካ አንፃር ይተነትናሉ፡፡<br>• የሕዝብ ብዛት ዕድገት በማኅበራዊ አካባቢ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ከምስራቅ አፍሪካ አንፃር ይተነትናሉ፤ይዘረዝራሉ፡፡ | 4.1.1. **ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት** *(3 ክ/ጊዜያት)*<br>• የተፈጥሮ እጽዋት መጨፍጨፍ፣ ድርቅ፣ ርሃብ፣ የእርሻ መሬት እጥረትና መበጣጠስ የሚያስከትሉት ችግር<br>• የምግብና መጠለያ እጥረት፣ አለመረጋጋትና የአካባቢ መበከል | • ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና ፍልሰት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን መወያየት፣<br>• በድርቅ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት የተከሰተ የመጠለያ ችግርን የሚያሳይ ውስን ጥናት ወይም ዘገባ ማቅረብ፡፡ ለምሳሌ በናይሮቢ ከተማ በህዝብ ጫና አማካይነት የተከሰተ የከተማ ቤት ችግር የተመለከተ ውስን ጥናት ወይም ዘገባ ማቅረብ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • እርስ በርስ ግጭት ወይም አለመረጋጋት፣ ስደትና፣ በስደተኞች መጠለያ ቦታ/ካምፕ/ ውስጥ መኖር የሚያሳይ ውስን ጥናት ወይም ዘገባ መተንተን፡፡<br>• የውሀ ብክለት ለምሳሌ የወንዝ፣ የሀይቅ ፣ የኩሬ፣ በአካባቢያቸው የሚኖሩ ግለሰቦችን ቃለ መጠይቅ አድርገው ውስን ጥናት ወይም ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>• በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የምግብ ምርት መቀነስና በአንፃሩ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ያላቸውን ትስስር አንድ አካባቢን በመውሰድ ውስን ጥናት አቅርቦ ማስረዳት፡፡ |
| • ስለ መሰረታዊ የሕፃናት መብቶች ምንነት ይገልፃሉ፡፡<br>• በኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች ጥሰት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ይገልጻሉ፡፡ | **4.2. የሕፃናት መብቶችና አያያዝ** (3 *ክ/ጊዜያት)*<br>• የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ድንጋጌዎች | • ተማሪዎች ባለፉት የክፍል ደረጃዎች ስለ መሰረታዊ የሕፃናት መብቶች ከተማሩት የሚያስታውሱትን እንዲገልፁ መጠየቅ፣ ምላሻቸውንም ሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | • የሕፃናት መብቶች ጥሰት ምሣሌዎች ጠለፋ፣ የጉልበት ብዝበዛ፣ የሕገ ወጥ የሕፃናት ዝውውር ወዘተ… | • በሕፃናት አድን ድርጅቶች ፖስተር ላይ ከአንቀጽ 1-42 የተመለከቱትን የሕፃናት መብቶች ድንጋጌዎች ውስጥ የተወሰኑ አንቀፆችን በማንበብ መወያየት፣<br>• ስለ ሕፃናት መብቶች ጥሰት ምሣሌዎችን በማንሣት በክፍል ውስጥ መወያየት፡፡<br>• ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚታዩ የሕፃናት መብት ጥሰቶች መረጃ ሰብስበው አደራጅተውና ጽፈው ለክፍሉ እንዲያቀርቡ የቡድን ስራ መስጠት፣ ተማሪዎች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት፡፡<br>• በኢትዮጵያ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ አገሮች የሕፃናት መብቶች ጥሰት የሚያሳይ ውስን ጥናት ማንበብና መተንተን፣ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የሕፃናት መብቶችን ለማስከበር የሚረዱ መንገዶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡<br><br>• የአኩያ ግፊትን ይቋቋማሉ፣ | **4.2.1.የሕፃናት መብቶችን ማስከበሪያ ስልቶች**<br>*(2 ክ/ጊዜያት)*<br>• መቃወም፣መሸሽ ማሳመን<br>• የአቻንን ግፊትና ጫና መመከት | • በቤተሰባቸው ውስጥ በጎረቤቶቻቸው ወይም በቀበሌያቸው ያዩት የጠለፋ ሙከራ፡ ወይም ሌላ አይነት የመብት ጥሰት ካለ በውስን ጥናት አማካይነት እንዲቀርብ ማድረግ፡፡<br>• በመቀጠልም የሕፃናት መብቶችን የማስከበሪያ ስልቶችን ላይ ውይይት ማድረግ፣<br>• ለምሳሌ የተሳሳተውን እንዳይቃወሙ፣ የሚያውቁትን እንዳይናገሩ በቤተሰባቸው ጫና ቢደረስባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወያየት፡፡ |
| • የድንገተኛ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡<br>• ድንገተኛ አደጋዎች ቢያጋጥሟቸው እንዴት እንደሚፈቱ ይገልጻሉ፡፡<br>• በድንገተኛ አደጋ ለተጐዳ ሊደረግ ስለሚገባ የመጀመሪያ እርዳታ ይገልፃሉ፡፡ | **4.2.2.ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባሮችና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች**<br>*(2 ክ/ጊዜያት)*<br>• ኮረንቲ(ኤሌክትሪክሲቲ)<br>• መርዛማ ነገሮች<br>• እሳት<br>• ተቀጣጣይ ነገሮች (ለምሳሌ ማዕድን ቁፋሮ) | • የተለያዩ የአደጋ ዓይነቶችን ሰሌዳው ላይ መፃፍና ተማሪዎቹ ገጠመኛቸውን እንዲናገሩ አድርጎ በየስሩ መፃፍ፣ በማያያዝም አደጋን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል መግለፅ፣<br>• ተማሪዎች አደጋዎችን እንዴት አድርገው እንደሚያስወግዱ እንዲገልጽ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች አደጋ ቢከሰትባቸው ምን |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
| --- | --- | --- |
| | | ማደረግ እንዳለባቸው እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• በመጨረሻም አደጋን ለማስወገድ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን የያዘ በራሪ ፁሁፍና የግድግዳ ፓስተር ወይም ስእላዊ መግለጫ አዘጋጅተው ግድግዳቸው ላይ እንዲለጥፉ ማዘዝ፡፡ |
| • በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች ስምና ዓላማ ይገልጻሉ፡፡<br>• የምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉዊ ድርጅቶች ጂኦግራፊያዊ ክልልን ያመለክታሉ፡፡<br>• የአጋርነት የጋራ ጉዳዩች አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፡፡ | **4.3. የአጋርነት ጉዳዮች**<br>*(3 ክ/ጊዜ,ያት)*<br>• ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች (ኢጋድ፣ የአባይ ተፋሰስ አገሮች ትብብር)<br>• መልካአምድራዊ ሽፋን<br>• የአጋርነት ዓላማዎች | • በመጀመሪያ ምህፃረ ቃል ምንድን ነው ብሎ በመጠየቅ የሚያውቋቸውን ምህፃረ ቃሎች ሲናገሩ መፃፍና ማስተንተን፣<br>• ከዚያም እንደ ኢጋድ ያሉ ድርጅቶችን አዎንታዊ ና አሉታዊ ገፅታዎች መተንተን፣<br>• እንደ ኢጋድ ባሉ ድርጅቶች ውስጥ ሰለሚሰራ አንድ ግለሰብ በማውሳት ስለድርጅቱ ዓላማ ቃለ መጠይቅ የተደረገ መሆኑን ማቅረብ፡፡<br>• አጋርነትን የመፍጠርና የማጠናከርን ጠቀሜታ በዝርዝር ማስረዳት፡፡<br>• ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መጠየቅና ግብና ዓላማ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ጠቀሜታውንም አክሎ ማስረዳት፡፡<br>• ለምሳሌ አንድ የእግር ኳስ ክለብ አሸናፊ ለመሆን ቢፈልግ የክለቡ ተጫዎቾች ተናበው ይጫወታሉ ግባቸው ማሸነፍ ነውና፡፡ከዚያም ማንኛውም ሰው ስለሚያከናውነው ተግባር ቀድሞ ማቀድና መወሰን ያስፈልጋል፡፡ |

## ***ምዘናና ግምገማ***

***መምህሩ/ሯ እያስተማረ/ች የያዘውን ምእራፍ እስኪያጠናቅቁ ድረስ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ብቃት በተከታታይ ይገመግማሉ፡፡ የግምገማ ውጤቱንም ከተጠበቀው ውጤት አንፃር በማየት ተማሪው የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ ማሟላት አለማሟላቱን ይወስናሉ፡፡ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያውን የሚያሟሉ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ፡-***

- ***ኤች አይቪ/ኤድስን በመከላከል ረገድ የህብረተሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ፣***
- ***ከኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ ጋር ከሚኖሩ ህፃናትና ቤተሰቦቻቸው ጋር በማህበራዊ ግንኙነት አብሮ የመኖርና የመማር ዝንባል ማሳየት፣***
- ***ከኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ወገኖችን ሳያገልሉና ሳያዳሉባቸው በምትኩ መንከባከብና ድጋፍ ማድርግ የዜግነት ሀላፊነት መሆኑን ይቀበላሉማሳየት፣***
- ***ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት በተፈጥሮ ሀብትና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይየሚያሰከትለውን ጫና ከምስራቅ አፍሪካ አኳያ መግለፅ፣***
- ***ለህፃናት መብቶች መገለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ሁንታዎችን መግለፅ፣***
- ***መብቶቻቸው እንዳይጣሱ መታገል፣***
- ***በምስራቅ አፍሪካ አገሮች ትብብር የተመሰረቱ ድርጅቶችን ይለያሉ፣አባል አገራትንም መጥራት፣***
- ***የምስራቅ አፍሪካ አገሮች የትብብር ግንኙነቶች ዓላማዎችን መግለፅ፣***
- ***በአገሮች መካከል የትብብር ግንኙነቶች አስፈላጊነቶችን መረዳት፡፡***

***ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የመማር ማስተማር ውጤት በላይ የሚያመጡ ተማሪዎች ይበረታታሉ፡፡ ውጤታቸውም ለበለጠ ስራ እንዲያበቃቸው ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በታች የሚያመጡ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍና ርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የተለየ ትኩረት ሊደረግላቸው፣ በእረፍት ሰዓትና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪም ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡***

# ምዕራፍ አንድ

## የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ፣ ሕዝቦችና አሠፋፈር

***ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡- 19***

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-***

***ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-***

- የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን መገኛ ይለያሉ፡፡
- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ጥንታዊ ሥልጣኔዎችንና ቅርሶችን ያደንቃሉ፡፡
- ቅርሶችን የመንከባከብ አስቸጋሪነትን ይገልጻሉ፡፡
- በምሥራቅ አፍሪካ የሕዝብ አሠፋፈርና አኗኗር ላይ አየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብቶች ያላቸውን ተጽዕኖ ያገናዝባሉ፡፡

***የምዕራፉ አደረጃጀት/ የምዕራፉ ዐበይት ይዘቶች***

- የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ
- የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች
- በመካነ ቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች
- የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች አሠፋፈርና አኗኗር
- በሕዝቦች አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ተጽእኖ የሚሳያድሩ ሁኔታዎች

### 1.1. የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮችና አንፃራዊ መገኛ

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-3***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- የምሥራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ ይገልጻሉ::
- የምሥራቅ አፍሪካን አገሮች ይዘረዝራሉ::

ሰ. ይዘቶች

- የምሥራቅ አፍሪካ አንፃራዊ መገኛ
- የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች

ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

አንፃራዊ መገኛ የታወቁ አመላካች ነጥቦችን ይጠቀማል፡፡ እንዲህ ያሉት ነጥቦች የመሬት ገጽታዎችን እና የውኃ አካላትን ያጠቃልላሉ፡፡ የምሥራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ ለመወሰን ኩታገጠም ሆነው የሚገኙ የመሬት ገጽታዎችንና የውኃ አካላትን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በላይ አንፃራዊ መገኛን ለመግለጽ ዋንኞቹን አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ ምሥራቅ አፍሪካ ከሕንድ ውቅያኖስ በስተምዕራብ፣ ከቀይ ባሕርና ከኤደን ባሕረ ሰላጤ በስተደቡብ ምዕራብ፣ ከሱዳን በስተምሥራቅና በስተደቡብ ምሥራቅ፣ ከኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በስተምሥራቅና በስተሰሜን ምሥራቅ፣ ከቦትስዋና በስተሰሜን ምሥራቅና ከደቡብ አፍሪካ ሪፑብሊክ በስተሰሜን ይገኛል፡፡

ምሥራቅ አፍሪካ በርካታ አገሮችንና ደሴቶችን ይይዛል፡፡ አገሮቹ በጥቂቱ ኤርትራን፣ ኢትዮጵያን፣ ጂቡቲን፣ ሶማሊያን፣ ኬንያን፣ ታንዛንያንና ዩጋንዳን ያጠቃልሉ፡፡ በክልሉ ከሚገኙት ደሴቶች ደግሞ ሞሪሽስ፣ ሪዩንየን፣ ኮሞሮስ፣ ሲሸልስና ማዳጋስካር ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የምሥራቅ አፍሪካ ንድፍ ካርታ
- የምሥራቅ አፍሪካ ፖለቲካዊ ካርታ
- አትላስ
- ቻርት

## 2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

- ገለፃ
- ምልከታ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ
- የጥንድ ሥራ
- የግል ሥራ

## 3. ቅድመ ዝግጅት

- የአንፃራዊ መገኛን ትርጉም ዝግጁ አድርጉ
- በሰሌዳ ላይ የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ አዘገጃጀት ተለማመዱ
- ዋና አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦችን ወይም የኮምፓስ አቅጣጫን የሚያሳይ ቻርት ያዘጋጁ
- ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸው፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

- ተማሪዎች አንፃራዊ መገኛን እንዲተረጉሙ፣
- ተማሪዎች በሰጡት ትርጉም ላይ ተንተርሰው ትክክለኛውን ትርጉም በመስጠት፣
- የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ በሰሌዳ ላይ በመሥራት፣
- በንድፍ ካርታው ላይ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ከቀይ ባሕርና ከሕንድ ውቅያኖስ የሚዋሰኑትን የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን እንዲያመለክቱ በማድረግ ትምህርቱን ማስተዋወቅ ይችላሉ

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡት መግለጫዎችንና ሥዕሎችን በማገናዘብ የአንፃራዊ መገኛን ምንነት ይግለጹ

- ተማሪዎችን የቤታቸውን፣ የትምህርት ቤታቸውንና በአካባቢው የሚገኘውን ሆስፒታል አንፃራዊ መገኛ እንዲገልጹ ጠይቋቸው፡፡
- የአፍሪካን ፖለቲካዊ ካርታ በመጠቀም የምሥራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ አስረዱ
- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠውን ፖለቲካዊ ካርታ በመጠቀም በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ሀገሮችንና ደሴቶችን አሳዩ
- በሰሌዳ ላይ በተሠራ የምሥራቅ አፍሪካ ንድፍ ካርታ ላይ ሀገሮችና የውኃ አካላት እንዴት እንደሚመለከቱ በተግባር አሳዩ፡፡

## ሪ. ምዘናና ክትትል

### *1. ግምገማ*

የሚከተሉትን የሚመስሉ ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- አንፃራዊ መገኛ ምን ማለት ነው?
- የምሥራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ ለመግለጽ የምትጠቀሙባቸው ዋና ነጥቦች ምንድን ናቸው?
- የምሥራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛ የሚወስኑትን የመሬት ገጽታዎችና የውኃ አካላት ግለጹ፡፡
- በቻርት ላይ የቦታዎችን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዋና አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦችን አመልክቱ
- የምሥራቅ አፍሪካ አንፃራዊ መገኛ ምንድን ነው?
- የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮችንና ደሴቶችን ዘርዝሩ

### 2. *ክትትል*

ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በመከፋፈል የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ጠይቋቸው፡፡

- በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ተግባራዊ ክንውኖች ሥሩ
- የአፍሪካን ንድፍ ካርታ በመጠቀም፦ ሰሜን ሱዳንን፣ ደቡብ ሱዳንን፣ የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን፣ ቦትስዋናንና የደቡብ አፍሪካን ሪፐብሊክ አመልክቱ

* የሕንድ ውቅያኖስን፣ ቀይ ባሕርንና የኤደን ባሕረ ሰላጤን አሳዩ
* የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮችን አመልክቱ
* የኢትዮጵያን፣ የጂቡቲን፣ የሶማሊያን፣ የኤርትራንና የኬንያን ዋና ከተማዎች አመልክቱ
* ለዋና ዋናዎቹ የውኃ አካላት አዋሳኝ የሆኑትን አገሮች አመልክቱ።

## 1.2. የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች

**የክፍለ ጊዜ ብዛት:- 4**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ:-

* የኑቢያን ሥልጣኔ ቀደምትነትና መለያ ገጽታዎቹን ከአክሱም ሥልጣኔ አንፃር ይገልፃሉ።
* በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ዋና ዋና ጥንታዊ ሥልጣኔዎችንና ቅርሶችን ይለያሉ::

### ለ. ይዘቶች

* የኑቢያና የአክሱም ጥንታዊ ሥልጣኔዎች
* የኑቢያ ሥልጣኔ
* የአክሱም ሥልጣኔ

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

በምሥራቅ አፍሪካ ሁለት የጥንታዊ ሥልጣኔ ማዕከላት ነበሩ። እነሱም ኑቢያና አክሱም በመባል ይታወቃሉ።የእነዚህ የጥንታዊ ስልጣኔ ማዕከላት አሻራዎች በአሁኑ ጊዜ በክልሉ ይስተዋላሉ።

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

* የአፍሪካ ታሪካዊ ካርታ
* አግባብ ያላቸው ፎቶግራፎች
* ሥዕሎች

2. *የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴዎች*
   - ውይይት
   - ሪፖርት አጻጻፍ
   - የመስክ ጉብኝት

3. ***ቅድመ ዝግጅት***
   - በትምህርቱ ንዑስ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ
   - በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ባሻገር ተጨማሪ ክንውኖች ማዘጋጀት
   - በማስተማሪያ መሣሪያዎች ጥቆማ ሥር የተዘረዘሩትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ እንዲገኙ ማመቻቸት

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

1. ***ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

   የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡
   - ኑቢያ የት ትገኛለች?
   - አክሱም የት ትገኛለች?
   - የአክሱም መንግሥት ዋናዋናዎቹ የምጣኔ ሀብት ክንዋኔዎች ምን ምን ነበሩ?
   - የአክሱም ሥልጣኔ ታዋቂ ቅርሶች ምንድን ናቸው?

2. ***የትምህርቱ አቀራረብ***
   - በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረበው ትምህርትና ሥዕላዊ መግለጫ አንፃር የኑቢያንና የአክሱምን አንፃራዊ መገኛ ያብራሩ
   - የኑቢያንና የአክሱምን ሥልጣኔዎች ዋናዋና ቅርሶች ይግለጹ
   - ተማሪዎች የአክሱምንና የኑቢያን ሥልጣኔዎች እንዲያነፃጽሩ ያበረታቷቸው
   - ተማሪዎች በቡድን ተቀናጅተው በኑቢያና በአክሱም ሥልጣኔዎች ላይ አግባብ ያላቸው መረጃዎችን እንዲጠቀሙና ያገኙትንም መረጃ ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ ይርዷቸው፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያቅርቡ፡፡

- የአክሱም ሥልጣኔ መቼ ተጀመረ?
- የአክሱም ሕዝብ ዋናዋና የምጣኔ ሀብት ክንዋኔዎች ምን ምን ነበሩ?
- የኑቢያ ሥልጣኔ አድጎ የነበረው የት አካባቢ ነበር?
- የአክሱም ሥልጣኔ ለምን ወደቀ?

*2. ክትትል*

ክፍሉን በሁለት ቡድን መድቡና እያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን እንዲፈጽም ያድርጉ፡፡

- በአፍሪካ ታሪካዊ ካርታ ላይ ኑቢያና አክሱምን አመልክቱ፡፡
- የኑቢያና የአክሱም ሥልጣኔዎችን ዋናዋና ቅርሶች ዘርዝሩ

## 1.3 በመካነ ቅርስ አጠባበቅና እንክብካቤ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፦ 2**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፦

- በመካነ ቅርሶች ላይ የተጋረጡ ችግሮችን ይለያሉ፡፡
- በመካነ ቅርሶች አጠባበቅ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይገልጻሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የቅርስ ዓይነቶች
- መካነ ቅርስ
- መካነ ቅርስና ቅርሶችን መጠበቅና መንከባከብ
- ጎብኚዎችን ማስተማር

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

ቅርሶች መንፈሳዊና ቁሳዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በአጠቃላይ መካነ ቅርስ ቅርሶች የሚገኙበት ሥፍራ ነው፡፡ ቅርሶች የገቢ ምንጮች

ናቸው። ስለዚህ ነዋሪ ሕዝቦች በአካባቢያቸው የሚገኙትን ቅርሶች እዲጠብቁ ማነቃቃትና ማስተማር ያስፈልጋል። ከዚህም በላይ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታም አላቸው። የቅርስ መገኛ አካባቢዎች ልዩ ልዩ ችግሮች እያጋጠሟቸው ነው። ከእነዚህም ውስጥ ዘረፋ፣ ብክለትና ውድመት ቀዳሚዎቹ ናቸው። ቅርሶችንና የቅርስ መገኛ አካባቢዎችን ለመመልከት የሚመጡ ሰዎችን በማስተማርና ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ቅርሶችን መጠበቅና መንከባከብ ይቻላል።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- ታሪካዊ ካርታዎች
- አግባብ ያላቸው ፎቶግራፎች

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ውይይት
- ሪፖርት አጻጻፍ
- የመስክ ጉብኝት

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- በትምህርቱ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ
- ተማሪዎች በትምህርቱ ርዕስ ላይ እንዴት ተጨማሪ ንባብ ማካሄድ እንዳለባቸው ሁኔታዎችን ያመቻቹ
- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ባሻገር ለቡድንና ለጥንድ ውይይት የሚያመቹ ርዕሶችን ያዘጋጁ
- የመማሪያ ማጣቀሻ መረጃዎች ያሰባስቡ ወይም ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው

- ቅርሶች ምንድናቸው?
- ቅርሶች የተወሰነ ሕዝብ ወይም አገር ሀብት ናቸው? ለምን?

- ዩኔስኮ እንደ ዓለም አቀፍ ሀብት የመዘገባቸውን በኢትዮጵያ የሚገኙ ቅርሶችን ዘርዝሩ፡፡
- በኢትዮጵያ ሕገወጥ አደን ተከልክሏልን? ለምን?

2. ***የትምህርቱ አቀራረብ***
   - በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ከተሰጠው ማብራሪያና ሥዕላዊ መግለጫ አንፃር በቅርስምንነትና ዓይነቶች፣በቅርስ መገኛ አካባቢዎች ላይ መግለጫ ይስጡ
   - በታሪካዊ ካርታ አማካይነት በኢትዮጵያ የሚገኙ የቅርስ መገኛ አካባቢዎችን ያሳዩ፡፡
   - በመንፈሳዊና በቁሳዊ ቅርሶች መካከል ያለውን ልዩነት ያብራሩ፡፡ ምሳሌዎችም ይስጡ
   - በኢትዮጵያ የሚገኙ የቅርስ መገኛ አካባቢዎችን የሚያመለክቱ አግባብ ያላቸው ፎቶግራፎች በመጠቀም ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
   - ስታስቲካዊ መረጃዎችን በመጠቀም በኢትዮጵያ የቱሪዝምን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታና የወደፊት እድገቱን ያብራሩ
   - በቅርሶች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና የችግር መፍቻ ዘዴዎችን ያስረዱ፡፡
   - ተማሪዎች ሰዎች የቅርስ መገኛ አካባቢዎችን ሲጎበኙ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያብራሩ በራሪ ጽሑፎች እንዲያዘጋጁ ይርዷቸው፡፡

**ሪ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- ለኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት የቅርስ አስፈላጊነት ምንድን ነው?
- በአክሱም ስለሚገኙ ዋና ዋና ቅርሶችና የቅርስ መገኛ አካባቢዎች አብራሩ
- በቅርሶችና በቅርስ መገኛ አካባቢዎች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ግለጹ

## 2. ክትትል

- ቅርሶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያስችሉ መመሪያዎች አዘጋጁ።
- ከዚህ አንፃር ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ያዘጋጅቱን ለክፍል ውይይት እንዲአቀርቡ ያድርጉ
- ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን ወይም ጥንድ የሚከተለውን እንዲፈጽም አድርጉ
- ቅርስን ከመጠበቅና ከመንከባከብ አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችንና መወሰድ ያለባቸውን እርጃዎች ዘርዝሩ።
- የቅርስ ዓይነቶች ዝርዝር አዘጋጁ
- የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ቁሳዊ ቅርሶተ ቻርት ሥሩ

## 1.4. የሕዝብ አሰፋፈርና አኗኗር በምሥራቅ አፍሪካ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፦ 6**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኂላ፦

- በምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሠፈረባቸውን አካባቢዎች ይለያሉ።
- በምሥራቅ አፍሪካና ኢትዮጵያ የሕዝቦች ፍልሰትና እንቅስቃሴ መንስኤንና ውጤቶችን ይገልጻሉ።
- በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በታንዛንያ ደጋማ አካባቢዎች ከፍተኛ ሥፍራዎች ላይ የሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ የሆነባቸውን ምክንያቶች ይለያሉ።
- በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት የሚኖረውን ተፅዕኖ ይገልጻሉ።
- የከተሞች መስፋፋት በባህልና ማኅበራዊ ለውጥ አንፃር የሚያመጣውን ለውጥ ይዘረዝራሉ።

**ሰ. ይዘቶች**

- የሕዝቦች አሠፋፈር
- የሕዝብ አሠፋፈርን የሚወስኑ ምክንያቶች
- የሕዝብ እንቅስቃሴ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች
- የከተሞች መስፋፋት በኅብረተሰብና በባህል ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

በምሥራቅ አፍሪካ የሕዝብ ቁጥር ከቦታ ወደ ቦታ ይለያያል፡፡ ከዚህም ክልሉ የተስተካከለ የሕዝብ ስርጭት እንደሌለው መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና ከሌሎች የአኅጉሩ ክልሎች ጋር ሲወዳደር ምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር አለው፡፡

ከዝቅተኛና መካከለኛ ሙቀትና ከፍተኛ የዝናብ መጠን አኳያ ሲታዩ የምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ሥፍራዎች ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት አላቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ከፍተኛ ሙቀትና ዝቅተኛ የዝናብ መጠን የሚስተዋልባቸው ዝቅተኛ ሥፍራዎችና የወንዝ ሸለቆዎች ዝቅተኛ የሕዝብ ጥግግት ይኖራቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በምሥራቅ አፍሪካ የሕዝብ ሥርጭት ሲመረመር ቀላል ኢንዱስትሪዎችና ቱሪዝም ገነው በሚታዩባቸው የጠረፍ አካባቢዎች ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ይስተዋላል፡፡

የሕዝብ ስርጭት ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ምክንያቶች ይኖሩታል፡፡
በሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ላይ ሁለት ዋናዋና ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ሰዎች መኖሪያ አካባቢዎችን እንዲለቁ የሚያደርጉና ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሳቡ ምክንያት የሚሆኑ ናቸው፡፡ ሰዎች መኖሪያ አካባቢያቸውን እንዲለቁ የሚያደርጉት የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ የአየር ንብረት ለውጦች የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎች ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሳቡ

ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች ውስጥ የሥራና የትምህርት ዕድል ማግኘት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በምሥራቅ አፍሪካ ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ በከፍተኛ ሁኔታ አድጓል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የከተማ አካባቢዎች በገጠር የሚኖሩ ሰዎችን የሚስቡ ማዕከላት ናቸው፡፡

ሰዎች ከአንድ የገጠር አካባቢ ወደ ሌላ የገጠር አካባቢ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ እውን የሚሆነው ሰዎች ለቤት እንስሳት የግጦሽ ሥፍራ ፍለጋና የተሻለ የእርሻ ሥፍራ ለማግኘት በሚያደርጉት ዝውውር ነው፡፡

- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በሕዝብ ብዛት ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡ የሕዝብ ቁጥር ያለቁጥጥር ከጨመረ በአንድ አካባቢ በሚገኝ አቅርቦትን ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ ችግሮች ያስከትላል
- የከተሞች ማደግ በሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በከተማ የሚኖሩ ሰዎች ሕይወት የተመሠረተው ከግብርና ውጭ ባሉ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው፡፡ በከተማ አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም ከገጠር አካባቢዎች በጣም የተለየ ነው፡፡ በአጠቃለይ የከተሞች መስፋፋት በአካባቢው ኅብረተሰብና ባህል ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

በምሥራቅ አፍሪካ ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ በግልጽ ይታያል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ሥራ ለማግኘት፣ ለመማርና የተለየ ሕይወት ለመምራት ከገጠር ወደ ከተማ ይፈልሳል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ እንቅስቃሴዎች በከተማ አካባቢዎች የሕዝብ ብዛትና ባህል ላይ ያልታሰበ ለውጥ ያስከትላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ሥራ አጥነት በከተሞች አካባቢ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ይህ ደግሞ ማኅበራዊ ቀውስ ያስከትላል፡፡

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

#### *1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የምሥራቅ አፍሪካ ንድፍ ካርታ
- የምሥራቅ አፍሪካ ፓለቲካዊ ካርታ

- አትላስ
- ቻርቶች

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- ገለፃ
- ምልከታ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ
- የጥንድ ሥራ
- የግል ሥራ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የተጠቀሙትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ያሳዩ
- ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሉ
- በዋቤነት የሚያገለግሉ በጣም አግባብ ያላቸው መረጃዎች ሰብስቡ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው

- የሕዝብ ስርጭት የሚለውን ንዑስ ሃረግ አብራሩ
- ለሕዝብ ስርጭት ምክንያት የሆኑትን እውነታዎች ዘርዝሩ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት የሚያስከትለውን ተጽእኖ አስረዱ፡፡
- የከተማ እድገት በኅብረተሰብና ባህል ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ አብራሩ
- የከተማ ዕድገት በምግብ ፍላጎትና አቅርቦት ላይ ያለውን ተጽእኖ አስረዱ፡፡

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ከተገለጸው አንፃር በምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛና አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውን ሥፍራዎች ያብራሩ

- ለሕዝብ ከቦታ ወደቦታ መዘዋወር ምክንያት የሆኑትን እውነታዎችና የሚያስከትሉትን ተጽእኖ ይግለጹ፡፡ ይህንን የሕዝብ እንቅስቃሴ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የኦሮሞ ሕዝቦች ካደረጉት እንቅስቃሴ ጋር በማነፃጸር ያብራሩ
- ለሕዝብ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ቁልፍ ምክንያቶች የሆኑትን ይተንትኑ
- የከተማ ዕድገት በኅብረተሰብና በባህል ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ያብራሩ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላሉ፡፡

- ሕዝብ ምን ማለት ነው?
- በሕዝብ ስርጭትና ለስርጭቱ መንስኤ በሚሆኑ ምክንያቶች ላይ ተወያዩ
- ለሕዝብ ከቦታ ወደቦታ መዘዋወር መንስኤው ምንድን ነው? ውይይታችሁን በምሳሌዎች ደግፉ
- ፈጣን የሕዝብ እድገት በመሬት አጠቃቀም፣ በመኖሪያ ቤትና በምግብ አቅርቦት ላይ የሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች ምንድን ናቸው?

2. ***ክትትል***

ክፍሉን በቡድን ወይም በጥንድ ከፋፍሉና እያንዳንዱ ቡድን ወይም ጥንድ የሚከተለውን እንዲሠራ አድርጉ፡፡

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡትን ተግባራዊ ክንዋኔዎች ሥሩ
- የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ አዘጋጅታችሁ፡-
  - ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር
  - ዝቅተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውን ሀገሮች አመልክቱ
  - ከመኖሪያ አካባቢያአችሁ ወደሌላ አካባቢ ስለሚፈልሱ ሰዎች አጥንታችሁ ግኝታችሁን ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## 1.5. በሕዝቦች አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ተጽእና የሚያሳድሩ ሁኔታዎች

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 4**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በሕዝቦች አሠፋፈርና አኗኗር መለያየት ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው ሁኔታዎችን ይተነትናሉ
- የፖለቲካ አለመረጋጋትና የእርስ በእርስ ጦርነት /ግጭት/ በሕዝብ ላይ ያለውን ተጽእኖ ይገልጻሉ

### ለ. ይዘቶች

- አየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት
- የፖለቲካዊ አለመረጋጋትና የእርስ በእርስ ጦርነት

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳቦች

ሠፈራ የሚለው ቃል ለሰዎች አኗኗር የሚያስፈልጉትን እንደ ቤት፣ ሕንፃ፣ ሠፈር፣ ትናንሽና ትላልቅ ከተሞች ያሉትን ያጠቃልላል። መገኛ፣ መገኛው የሚገኝበት አቅጣጫ፣ ቅርሱ፣ መጠኑ፣ የሕዝብ ስርጭትና የሕዝብ አሠፋፈር ሁኔታ ከካርታ ላይ ሊገኝ ይችላል።

የሕዝብ አሠፋፈር በከተማና በገጠር ተብሎ ሊከፈል ይችላል። የገጠር አሠፋፈር መሠረቱ ግብርና ነው። የከተማ አሠፋፈር መሠረቶች ከግብርና ውጭ የሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በገጠር የሚኖሩ ሰዎች የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። በከተማ የሚኖር ሕዝብ ግን እንደገጠሩ የሚቀራረብ አይደለም። ላይተዋወቅም ይችላል። በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኘው ሕዝብ በከተማና በገጠር የሚኖር ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የሕዝብ አሠፋፈር ሥርአታዊነትንና የአኗኗር ዘይቤን የሚወስኑ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። እነዚህ ምክንያቶች፡-

- አየር ንብረትንና የተፈጥሮ ሀብትን
- የፖለቲካ አለመረጋጋትንና የእርስበእርስ ጦርነትን ያጠቃልላሉ።

መካከለኛ ሙቀትና ወቅቱን ጠብቆ የሚጥል ዝናብ ባለው አየር ንብረት የሕዝብ አሠፋፈር የተረጋጋ ነው፡፡ ይህ አሠፋፈር የገጠር ወይም የከተማ ሊሆን ይችላል፡፡ በእነዚህ በተለያዩ አሠፋፈሮች ሁለት የተለያዩ እንደውም የሚቃረኑ የባህል እድገቶች ይስተዋላሉ፡፡ እነሱም የገጠር ባህልና የከተማ ባህል ናቸው፡፡

የሀብት መገኘት ወይም መትረፍረፍ በአሠፋፈር ዓይነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለምሳሌ የለም አፈር መኖር ግብርና እንዲስፋፋ ምክንያት ይሆናል፡፡ ማዕደን በተገኘበት ደግሞ ግብርና ነክ ያልሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ሊስፋፉ ይችላሉ፡፡

የመሬት አቀማመጥም የሕዝቦች አኗኗርን ከሚወስኑ እውነታዎች አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ በከፍተኛ ሥፍራ የሚኖሩ ሰዎች የምግብ እህል ከማብቀሉ ጎን ለጎን እንስሳት በማርባት ሕይወታቸውን ይመራሉ፡፡ በዝቅተኛ ሥፍራ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ በአብዛኛው እንስሳት በማርባት ኑሮአቸውን ይገፋሉ፡፡

የሕዝብ አሠፋፈር ሥርዓታዊነት በፖለቲካ አለመረጋጋትና በእርስ በእርስ ጦርነት ሊሸረሸር ይችላል፡፡ መንግሥታት ባልተረጋጉበትና የእርስ በእርስ ጦርነት በተበራከተበት ሰዎች መኖሪያ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ማይታወቅ አካባቢ እንዲፈልሱ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ በሶማሊያና በኤርትራ ይስተዋላል፡፡ በዚህም ምክንያት አያሌ ሕዝቦች አገራቸውን እየለቀቁ በኢትዮጵያና በኬንያ በመሥፈር የአካባቢውን የገጠርና የከተማ ነዋሪ ሲያጨናንቁ ይስተዋላል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የምሥራቅ አፍሪካ ፖለቲካዊ ካርታ
- አትላስ

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- ገለፃ
- ውይይት
- ምልከታ
- የቡድን ሥራ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የተጠቀሙትን የትምህርት መሣሪያዎች በማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ
- በምሥራቅ አፍሪካ በሚስተዋሉት የእርስ በእርስ ጦርነቶችና በፖለቲካ አለመረጋጋት ላይ ተጨማሪ መረጃዎች አሰባስቡ
- ክፍሉን በቡድን ይከፋፍሉ፤

**ሠ. *የመማር ማስተማር ሂደት***

1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ
2. የትምህርቱ አቀራረብ

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡

- በኢትዮጵያ የከፍተኛ ሥፍራ ነዋሪዎችንና በኬንያ የዝቅተኛ ሥፍራ ጠረፍ አካባቢ ነዋሪዎችን አነፃጽሩ
- የአሠፋፈርና የአኗኗር ልዩነት የሚፈጥሩትን ምክንያቶች ዘርዝሩ
- በሕዝብ አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ልዩነት በመፍጠር ቀዳሚ ሚና የሚኖራቸውን አየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት አብራሩ፡፡
- በምሥራቅ አፍሪካ በሕዝብ አሠፋፈር እና አኗኗር ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩት በፖለቲካ አለመረጋጋትና በእርስ በእርስ ጦርነት ላይ ተወያዩ፡፡
- በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራ የሚስተዋለውን የሕዝብ አሠፋፈር ሥርዓታዊነትና በኬንያ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ጠረፍ አካባቢ (ጊሪያማ) የሚኖረውን ሕዝብ አሠፋፈር አነፃጽሩ፡፡ በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰውን ውስን ጥናት ይመልከቱ
- በምሥራቅ አፍሪካ ካርታ ላይ በእርስ በእርስ ጦርነት ወይም በፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም በሁለቱም የተጠቁትን አካባቢዎች አመልክቱ

- ከሌሎች ሥፍራዎች ወደ ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ዩጋንዳ መጥተው በሚሠፍሩ ሰዎች ምክንያት በተቀባይ አገሮች ላይ የተፈጠረውን ሁኔታ ያብራሩ
- በፖለቲካ አለመረጋጋትና በእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት በምሥራቅ አፍሪካ የተፈጠረውን የአሠፋፈርና የአኗኗር መለያየት ያስረዱ፡፡
- በምሥራቅ አፍሪካ በአሠፋፈርና በአኗኗር ላይ ልዩነት የሚፈጥሩ ምክንያቶች ምንድናቸው?
- በምሥራቅ አፍሪካ ለሕዝብ አሠፋፈርና አኗኗር መለያየት ምክንያት በሆኑት በአየር ንብረትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተወያዩ
- ሰዎች ለምን ከሶማሊያ ወደ አጎራባች አገሮች ይፈልሳሉ?
- ወደ ተቀባይ ሀገሮች የሚመጡ ስደተኞች በተቀባይ ሀገሮች የሕዝብ ቁጥር ላይ የሚያስከትሉትን ተጽእኖ አብራሩ

**2. *ክትትል***

ክፍሉን በቡድን ወይም በጥንድ ይከፋፍሉና እያንዳንዱ ቡድን ወይም ጥንድ የሚከተለውን እንዲሠራ ያድርጉ፡፡

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡትን ክንውኖች ሥሩ
- በምሥራቅ አፍሪካ ንድፍ ካርታ ላይ፡-
    - ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውን አካባቢዎች
    - በእርስ በእርስ ጦርነቶችና በፖለቲካ አለመረጋጋ የተጎዱትን አካባቢዎች
    - የኬንያን ጠረፍ አካባቢዎች አመልክቱ
    - በፖለቲካ አለመረጋጋት እና በእርስ በእርስ ጦርነት ላይ የተዘጋጁ ተጨማሪ ጽሑፎች በማንበብ ግኝታችሁን ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

**ሀ. እውነት ወይም ሐሰት**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት

**ለ. አዛምዱ**

6. ረ 7. ሀ 8. ለ 9.ሐ 10. ሸ

**ሐ. ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

11. መ 12. መ 13. ለ

**መ. ክፍት ቦታውን ሙሉ**

14. የቅርስ መገኛ አካባቢዎች/ መካነ ቅርስ
15. መንፈሳዊ ቁሳዊ ተብለው ይከፈላሉ::
16. የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብትና መልክ ዓምድራዊ አቀማመጥ

# ምዕራፍ ሁለት

## የምንኖርባት መሬት

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡- 19**

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች***

***ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ***

- የዓለምን አኅጉራትና የውኃ አካላትን ይለያሉ፣ ጨው አልባ ውኃንና ጨዋማ ውኃን ያነፃጽራሉ፡፡
- የምሥራቅ አፍሪካን የመሬት ገጽታዎች ይገልጻሉ
- የከባቢ አየር ንብርብሮችን ይለያሉ፤ የሥረሕዋ ጥንቅሮችን ይገልጻሉ፡፡
- ካርታ በመንደፍ ቅልመቶች፣ ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች በመጠቀም ልዩ ልዩ የመሬት ገጽታዎችን ማሳየት ይችላሉ፡፡

**የምዕራፉ አደረጃጀት/ የምዕራፉ ዐበይት ይዘቶች**

- የመሬት ገጽታ
- የምሥራቅ አፍሪካ ዋና ዋና የምድር ቅርጾች
- የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ሀብት
- የምሥራቅ አፍሪካ ውኃና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሙ
- ከባቢ አየር
- ዓለማቀፋዊ የካርታ ምልክቶችና ውክሎች(ወካይ ምልክቶች)

### 2.1 የመሬት ገጽታ

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የዓለምን አኅጉሮች ይዘረዝራሉ
- የዓለምን ዋና ዋና ውቅያኖሶች ስም ይጠራሉ

- የውኃ አካላት ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ
- የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ አካሎችን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታዎች ይዘረዝራሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- አኅጉራት
- የውኃ አካላት

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

የመሬት ገጽ መልክዓ ምድርንና የውኃ አካላትን ያጠቃልላል፡፡ መልክዓ ምድር በትላልቅ፣ በተያያዙ የየብስ አካላት የተከፋፈለ ሲሆን እነዚህ የየብስ አካላት አኅጉራት ይባላሉ፡፡ በዓለም ላይ ሰባት አኅጉራት አሉ፡፡ አንዳንዶቹ አኅጉራት ትላልቅ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በአንፃራዊ ሁኔታ አነስተኛ ናቸው፡፡

ሰባቱ አኅጉራት ከስፋታቸው አኳያ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡፡ ይኸውም እስያ፣ አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አንታርክቲካ፣ አውሮፓና አውስትራሊያ ናቸው፡፡

የውኃ አካላት በመሬት ገጽ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሲሆን መጠናቸውም የተለያየ ነው፡፡ ከጨው ይዘታቸው አኳያም የውኃ አካላት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ጨዋማና ጨው አልባ የውኃ አካላት ናቸው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

***1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***

- መልክዓምድራዊና ፖለቲካዊ የአፍሪካ ካርታ
- ንድፍ ካርታዎች

***2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች***

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

3. *ቅድመ ዝግጅት*

- ተማሪዎች እንዲያነቡ የቤት ሥራ ይስጧቸው
- የማስተማሪያ መሣሪዎችን በክፍል ውስጥ በቅደም ተከተል ያስቀምጡ
- አጫጭር ማስታወሻ ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

1. ***ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

ተማሪዎችን የሚተከሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ።

- አኅጉር ምን ማለት ነው?
- በዓለም ላይ ስንት አኅጉራት አሉ?
- ውኃ ምንድን ነው?
- የምታውቁአቸውን የውኃ አካላት ዘርዝሩ
- በአካባቢአችሁ ምን ዓይነት የውኃ አካላት ይገኛሉ?

2. ***የትምህርቱ አቀራረብ***

የዓለምን መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታ በመጠቀም፡-

- የዓለምን ዋና ዋና አኅጉራት አመልክቱ
- የዓለምን ውቅያኖሶችና ባሕሮች መገኛ አሳዩ
- የዓለምን ታላቁን ውቅያኖስ ስያሜ ተናገሩ
- አኅጉራትን በስፋታቸው ቅደም ተከተል ዘርዝሩ
- በጣም ትንሽ የጨው መጠን ባላቸው የውኃ አካላትና ጨዋማ የውኃ አካላት መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።
- የውኃን ጥቅም የሚገልጹ ምሳሌዎች አቅርቡ
- የዓለም ውቅያኖሶችን፣ ባሕሮችንና ሐይቆችን ጥቅም ያብራሩ
- ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ለእያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን ሥራ ስጡ።
    - የዓለምን ንድፍ ካርታ በማዘጋጀት የሚከተሉትን አመልክቱ።
        1. የዓለም አኅጉራትን
        2. የዓለም ውቅያኖሶችን
        3. የዓለም ዋና ዋና ባሕሮችን
        4. የዓለም ዋና ዋና ወንዞችን

- የእያንዳንዱ ቡድን ሥራ ይመርምሩ
- በመጨረሻም ትምህርቱን ያጠቃሉ

### ረ. ምዘናና ክትትል

*1. ግምገማ*

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

- የትኛው አኅጉር እጅግ በጣም ሰፊ ነው?
- አኅጉራትን በስፋታቸው መሠረት ዘርዝሯቸው
- የትኛው አኅጉር እጅግ በጣም ቀዝቃዛ ነው?
- ውቅያኖሶች ምንድናቸው?
- ውቅያኖሶች ከባሕሮች በምን ይለያሉ?
- በዓለም ላይ እጅግ በጣም ረዥም የሆነውን ወንዝ ስም ጥሩ
- የውኃ አካላትን ጥቅም ተናገሩ

*2. ክትትል*

ተማሪዎችን በቡድን ክፈሉና እያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን እንዲፈጽም ያድርጉ፡፡

- የዓለምን ንድፍ ካርታ ሠርታችሁ አኅጉራትን፣ ውቅያኖሶችን፣ ባሕሮችን፣ ሐይቆችንና ዋናዋና ወንዞችን አመልክቱ
- በውኃ አካላት ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ላይ ማስታወሻ ጻፉ፡፡

## 2.2፡ የምሥራቅ አፍሪካ ዋና ዋናዎቹ የመልክዓ ምድር ገጽታዎች

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 4***

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የምሥራቅ አፍሪካን ዋና ዋና የመልክዓ ምድር ገጽታዎች ይለያሉ::
- የታላቁን የምሥራቅ አፍሪካስምጥሸለቆ አመሠራረትና ጠቀሜታ ይተነትናሉ፡፡

**ሰ. ይዘቶች**

- የምሥራቅ አፍሪካ መልክዓ ምድር ገጽታዎች
- ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

የመልክዓ ምድር ገጽታዎች የመሬትን ገጽ ከፍና ዝቅ ማለት ያጠቃልላሉ፡፡ የመሬት ገጽ ከፍና ዝቅ ማለት ደግሞ በኮረብታዎች፣ በተያያዩ ጉብታዎች፣ በተራራዎች፣ በሸለቆዎች፣ በሜዳማ ሥፍራዎችና በመጠኑ ወጣ ገባ በሆኑ ሥፍራዎች ይካተታሉ፡፡ እነዚህ የመሬት ገጽታዎች ሁሉ በምሥራቅ አፍሪካ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አካባቢው ተራራዎች ገነው የሚታዩበት ነው፡፡

በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ሥፍራዎች ከፍታ 5895 ሜትሮች ከሚሆነው የኪሊማንጃሮ ጫፍ አንስቶ ከባሕር ጠለል በታች 120 ሜትር በሆነው የኮባር ስምጥ መካከል ተንጣለው ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አስደናቂው የክልሉ የመሬት ገጽታ ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥሸለቆ ነው፡፡ ይህ ሸለቆ በመካከለኛው ምሥራቅ ከሶሪያ አንስቶ በምሥራቅ አፍሪካ በስተደቡብ እስከምትገኘው ሞዛምቢክ የተዘረጋ ነው፡፡ ይህ ሥፍራ 7,200 ኪሎሜትር ርቀት ይሸፍናል፡፡ ከ5000 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ በአፍሪካ ውስጥ ተዘርግቶ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የዓለም መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታ
- የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታ
- ንድፍ ካርታ

*2. የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴዎች*

- የጥንድ ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

### *3. ቅድመ ዝግጅት*

- የምሥራቅ አፍሪካን መልክዓ ምድራዊ ካርታ ዝግጁ ያድርጉ
- በትምህርቱ ርዕስ ላይ ተገቢ ማስታወሻ ያዘጋጁ
- አሳታፊ ትምህርት ለማቅረብ የሚያስችሉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ምረጡ
- የግል፣ የጥንድ ወይም የቡድን ሥራ የሚያበረታቱ መልመጃዎች ይምረጡ ወይም ያዘጋጁ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. *ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ።

- መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች ምንድናቸው?
- ስምጥ ሸለቆ ምን ማለት ነው?
- ስምጥ ሸለቆ እንዴት ይመሠረታል?

### *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- በክፍል ውስጥ የአፍሪካን ካርታ በማቅረብ ተማሪዎች በካርታው ላይ፡-
  - የምሥራቅ አፍሪካ አገሮችን እንዲያሳዩ
  - የምሥራቅ አፍሪካ ደሴቶችን እንዲያመለክቱ
  - ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የሚነሳበትንና የሚደርስበትን አካባቢዎች እንዲናገሩ ጠይቋቸው
    - ➢ ከዚህ በኋላ ስምጥ ሸለቆው እንዴት እንደተመሠረተና ያሉትን ቅርንጫፎች አስረዱ
- ተማሪዎችን በተለያዩ ቡድኖች መድቡና እያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉትን እንዲያከናውን አድርጉ።
  - የአፍሪካን ንድፍ ካርታ በማዘጋጀት የምሥራቅ አፍሪካ አገሮችን አመልክቱ
  - የአፍሪካን ንድፍ ካርታ በማዘጋጀት በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ የከፍተኛ ሥፍራዎች ጫፎችና እነዚህ ጫፎች የሚስተዋሉባቸውን አገሮች በካርታው ላይ አሳዩ

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

- መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች ምንድናቸው?
- የተለያዩ የመልክዓ ምድር ገጽታዎች ተናገሩ
- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ከፍተኛ የተራራ ጫፎችን ዘርዝሩ
- ስምጥ ሸለቆ ምንድነው? እንዴት ይመሠረታል?
- የስምጥ ሸለቆ ጥቅም ምንድነው?

*2. ክትትል*

- ተማሪዎች በሚከተሉት ርዕሶች ላይ አጫጭር ማስታወሻ እንዲጽፉ ማድረግ ይችላሉ፡፡
  - የታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ አመሠራረት
  - ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የሚያካልላቸው አገሮች

**2.3፡- የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ሀብት**

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-** 2

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ወንዞችን፣ ሐይቆችና ባሕሮችን ይዘርዝራሉ::
- ጨዋማና ጨው አልባ የውኃ አካላትን ያነፃጽራሉ::

**ለ. ይዘቶች**

- የምሥራቅ አፍሪካ ወንዞች፣ ሐይቆችና ባህሮች
- ጨዋማና ጨው አልባ የውኃ አካላት

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

ምሥራቅ አፍሪካ በውኃ ሀብት የታወቀ ነው፡፡ በርካታ ወንዞችና ሐይቆች ይገኙበታል፡፡ ባሕርና ውቅያኖስ ግን በጣም ውስን ናቸው፡፡

በክልሉ አካባቢ ያሉት ባሕርና ውቅያኖስ ከክልሉ ጋር ኩታ ገጠም ናቸው። ባሕሩ ቀይ ባሕር ሲሆን ውቅያኖሱ ደግሞ ሕንድ ውቅያኖስ ነው።

በውኃ ሀብታቸው ማለትም በወንዞችና በሐይቆች የታወቁት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ዩጋንዳና ታንዛንያ ናቸው። በክልሉ በጣም ታዋቂ ወንዞችና ሐይቆች አሉ። ታዋቂዎቹ ወንዞች ነጭ አባይና ጥቁር አባይ ናቸው። ከሞላ ጎደል ሁሉም ሐይቆች የሚገኙት በታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው። በዚህም የተነሳ ሐይቆቹ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በመባል ይታወቃሉ።

የክልሉ የውኃ አካላት ጨዋማና ጨው አልባ የውኃ አካላት በመባል በሁለት ይከፈላሉ።

ጨዋማ ያልሆኑ የውኃ አካላት ወንዞችና ሐይቆችን ያጠቃልላሉ። ጨዋማ የውኃ አካላት ደግሞ በክልሉ ያሉትን ባህርና ውቅያኖስ ይይዛሉ።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ - ዘዴ**

***1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***

- የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታ
- ንድፍ ካርታዎች

***2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች ጥቆማ***

- ገለጻ
- የጥንድ ውይይት
- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

***3. ቅድመ ዝግጅት***

- ተማሪዎች አንብበው እንዲመጡ ያድርጉ
- አግባብ ያላቸው ካርታዎች ለእይታ ያብቁ
- የግል፣ የጥንድ ወይም የቡድን ሥራ የሚያበረታቱ መልመጃዎች ይምረጡ ወይም ያዘጋጁ።

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማቅረብ ይችላሉ፡፡

- በሐይቆች፣ በወንዞችና በባሕሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- የትኞቹ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች በውኃ ሀብታቸው የታወቁ ናቸው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

የአፍሪካን መልክዓ ምድራዊ ካርታ በመጠቀም ተማሪዎች፡-

- ምሥራቅ አፍሪካን የሚከቡ ወይም ክልሉን የሚነኩ የውኃ አካላትን እንዲያመለክቱ
- የምሥራቅ አፍሪካን ወንዞችና ሐይቆች እንዲያሳዩ ጠይቋቸው
- ክፍሉን በጥንድ ወይም በቡድኖች ከፋፍለው እያንዳንዱ ጥንድ ወይም ቡድን የሚከተለውን ሥራ እንዲያከናውን ያድርጉ፡-
  - የምሥራቅ አፍሪካን ሐይቆች በመዘርዘር ስፋታቸውንና ጥልቀታቸውን አብራሩ
  - የኢትዮጵያን ሐይቆች በመዘርዘር የስምጥ ሸለቆ፣ የእሳተ ገሞራ ቀሪዎችና የከፍተኛ ሥፍራ ሐይቆች በማለት ከፋፍሏቸው፡፡
  - የምሥራቅ አፍሪካን ታዋቂ ወንዞች በመዘርዘር የወንዞቹ ተፋሰሶች የሚነኩአቸውን ሀገሮች ግለጹ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡

- በአፍሪካ አብዛኛዎቹ ሐይቆች የት ይገኛሉ?
- በአፍሪካ ቃላቁ ሐይቅ ማን ይባላል?
- በምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ሀብት ምን ያህል ፍትሃዊ ሆኖ ተከፋፍሏል?

*2. ክትትል*

ለተማሪዎች የሚከተለውን እንዲሠሩ መንገር ይችላሉ፡፡

- የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ በመሥራት
  - የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችን
  - ቀይ ባሕርንና ሕንድ ውቅያኖስን አመልክቱ

## 2.4. የምስራቅ አፍሪካ ውኃና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሙ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 2**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በምሥራቅ አፍሪካ የውኃን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ይገልጻሉ::
- የውኃን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ በቁልፍ ምሳሌዎች ያስረዳሉ::
- ውኃ የአንድን አካባቢ ስትራተጂያዊ ተፈላጊነት እንደሚወስን ያብራራሉ::

**ለ. ይዘቶች**

- በምሥራቅ አፍሪካ ውኃና ምጣኔ ሃብታዊ ጥቅሙ

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

ውኃ የተፈጥሮ ስጦታ ነው፡፡ አያሌ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከውኃ ጥቅሞች አንዱ ለቤት ውስጥ አገልግሎት መዋሉ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ውኃ በቤት ውስጥ ምግብ ለመሰናዳት፣ለመጠጥነት፣ የምግብ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ለማጽዳትና ለግል ንጽህና አጠባበቅ ጥቅም ላይ ሲውል ይችላል፡፡

ውኃን ከሚይዘው ሥፍራ አንፃር ስናጠኔው በርካታ የሚታወቁና ለሀገር ምጣኔ ሀብት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጠቀሜታዎች እንዳሉት እንረዳለን፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ምሥራቅ አፍሪካ የወንዞችና የሐይቆች ሀብት አለው፡፡ እነዚህ የውኃ አካላት አሣ ለማስገር፣ የኤሌክትሪክ ሐይል ለማመንጨት፣ ለመስኖ እርሻና ለመጓጓዣነት ያገለግላሉ፡፡

ሰፋፊዎቹ ሐይቆች አሣ ለማስገርና ለመጓጓዣነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ወንዞች የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ያገለግላሉ። በክልሉ በጣም ውስን ወንዞች በየአካባቢው ለመጓጓዣነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ይሁን እንጂ አብዛኞዎቹ ወንዞች ለመጓጓዣነት አያገለግሉም። ምክንያቱም ከሞላ ጎደል ወንዞቹ በሙሉ ፏፏቴዎች ስላሏቸው ነው። በክልሉ ያሉ አንዳንዶቹ ወንዞች ድንበር አቋራጭ ናቸው። እነዚህን ወንዞች በጥንድ ወይም በጋራ የሚጠቀሙ ሀገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያስፈልጋቸዋል። አንዳንድ ጊዜ በጥንድ ወይም በጋራ ድንበር አቋራጭ ወንዞቹን በመጠቀሙ ላይ የተሳሳተ አስተሳሰብ በመያዝ ወይም በውል ባለመረዳት በተጠቃሚ ሀገሮች መካከል ግጭት ሊከሰት ይችላል። ነገር ግን በጥንድ ወይም በጋራ በወንዞቹ በሚጠቀሙ ሀገሮች መካከል የጋራ መግባባት ላይ ከተደረሰ ግጭቶች በቀላሉ ይወገዳሉ። በዚህም ምክንያት ወንዞቹ አካባቢን ለማልማት ጥቀም ላይ ይውላሉ።

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

#### *1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የምሥራቅ አፍሪካ መልክዓምድራዊ ካርታ
- የምጣኔ ሀብታዊ ክንዋኔዎች የሚያሳዩ የሐይቆች ፎቶግራፎች

#### *2. የማስተተማሪያ ሥነ ዘዴዎች ጥቆማ*

- ገለጻ
- ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልክታ

#### *3. ቅድመ ዝግጅት*

- የምሥራቅ አፍሪካን መልክዓምድራዊ ካርታ ዝግጁ ያድርጉ
- የቡድን ውይይት የሚያበረታቱ የትምህርት ንዑስ ርዕሶች ይምረጡ
- በውኃ አካላት ላይ የሚደረጉ ምጣኔ ሀብታዊ ክንውኖችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ሰብስቡ

- ወንዞችን የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት አኳያ የሚሰጡትን ጥቅም አስመልክቶ ምሳሌ በሚሆኑ ሀገሮች ላይ መረጃ አሰባስቡ

**ሠ. የመማር ማተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ።

- ከአሣ ማስገር፣ ከመስኖ አገልግሎትና ከመጓጓዣ አንፃር የምሥራቅ አፍሪካ ወንዞችንና ሐይቆችን አነፃጽሩ።
- ሐይቆች ለመስኖ አገልግሎት ይውላሉን? መልሳችሁ አዎ ከሆነ እንዴት?
- ከላይ ከተጠቀሱት የውኃ አካላት ለቤት ውስጥ ግልጋሎት የሚውሉበትን ጥቀሱ

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- ውኃ ለቤት ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት አብራሩ
- ወንዞች የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በሚሰጡት ጥቅም ላይ ተወያዩ
- ወንዞች ለአሣ ማስገር፣ ለመስኖ እና ለመጓጓዣ የሚሰጡትን አገልግሎት ጥቅም ዘርዝሩ
- ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን፡-
    - በምሥራቅ አፍሪካ ለመጓጓዣነት የሚውሉትን ወንዞች እንዲለዩ ያድርጉ
    - በምሥራቅ አፍሪካ ለምን ወንዞች የኤልክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ምቹ እንደሆኑ እንዲወያዩ ያድርጉ
    - ከታዋቂው የምሥራቅ አፍሪካ ሐይቅ ጋር ግንኙነት ያለውን የአሣ ማስገር ሥራ እንዲያብራሩ ይጠይቁ

## ረ. ምዘናና ክትትል

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡

- በኢትዮጵያ የውኃ አካላት ከሚሰጧቸው ጥቅሞች ጥቂቱን ዘርዝሩ
- ለአሣ ማስገርና ለመጓጓዣነት የሚያገለግሉትን ባሕሮች ጥቀሱ

*2. ክትትል*

ተማሪዎች የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ ሠርተው ለአሣ ማስገር ጠቀሜታ ላይ የዋሉ የውኃ አካላትን እንዲያመለክቱ ያድርጉ፡፡

## 2.5. ከባቢ አየር

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የከባቢ አየር ንብርብሮችን ይለያሉ::
- የከባቢ አየርን ታችኛው ክፍል ጥንቅሮች ያብራራሉ::
- የከባቢ አየርን ንብርብሮች የሚያሳይ ቻርት በመሥራት ስያሜዎችን ያሠፍራሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የከባቢ አየር ንብርብሮች
- የከባቢ አየር ታችኛው ክፍልና ጥንቅሮቹ

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

ከባቢ አየር የመሬትን ገጽ እንደብርድልብስ የሚሸፍን ነው፡፡ ይህ አየር የተለያዩ ጋዞች ድብልቅ ነው፡፡ የመሬት ከባቢ አየር በአራት ንብርብሮች ይከፈላል፡፡ እያንዳንዱ ንብርብር የራሱ መለያ ባህርያት አሉት፡፡ አራቱ የከባቢ አየር ንብርብሮች ትሮፖስፌር (ሥረሕዋ)፣ ስትራቶስፌር (ዝቀሕዋ)፣ ሜሶስፌር (መካ ሕዋ) እና ተርሞስፌር (ሙቀሕዋ) ይባላሉ፡፡ ከአንዱ ንብርብር ወደ ሌላው መሸጋገሪያ ንብርብሮች አሉ፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

1. ***የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***
   - የመሬትን ገጽ ቅርጽ የያዘ የከባቢ አየርን ንብርብሮች የሚያሳይ ምስል
   - ቻርት
   - ሥዕሎችና ፎቶግራፎች

2. ***የማስተማሪያ ሥነ  ዘዴዎች***
   - ጥያቄና መልስ
   - ገለጻ
   - ምልከታ
   - የጥንድ ውይይት
   - የቡድን ውይይት

3. ***ቅድመ ዝግጅት***
   - በከባቢ አየር ንብርብሮች ላይ ተጨማሪ መረጃ ሰብስቡ
   - የመሬትን ከባቢ አየር ሊገልጹ የሚችሉ ሥዕሎችና ምስሎች በክፍሉ ውስጥ ዝግጁ ያድርጉ
   - የግል፣ የጥንድ እና የቡድን ሥራ የሚያበረታቱ መልመጃዎችን አቀናጁ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

1. ***ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

   ለተማሪዎች የሚከተሉን ዓይነት ጥያቄዎች ያቅርቡ

   - ከባቢ አየር ምንድነው?
   - የከባቢ አየር ጥንቅሮች ምንድናቸው?
   - የአዮኖስፊርና የኦዞን ንብርብሮች የት እንደሚገኙ ጠቁሙ
   - የአዮኖስፊርና የኦዞን ንብርብሮች ስለሚሰጡት ጥቅም በስፋት ተወያዩ፡፡
   - ሥረሕዋ ጥንቅሮችን ዘርዝሩ

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

የመሬትን ከባቢ አየር ንብርብሮች የሚያሳየውን ምስል በመመልከት፡-

- የአየርን ጥንቅሮች አብራሩ
- የከባቢ አየር ንብርብሮችን ግለጹ
- ሥረሕዋ ጥንቅሮች አብራሩ

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው

- ከባቢ አየር ምን ማለት ነው?
- ከባቢ አየር ስንት ንብርብሮች አሉት?
- የአይኖስፌርና የኦዞን ንብርብሮች የት ይገኛሉ?

*2. ክትትል*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- የመሬትን ሞላላ ገጽ የያዘውን ምስል ሠርታችሁ የከባቢ አየር ንብርብሮችን አሥፍሩ
- በእያንዳንዱ የከባቢ አየር ንብርብር ላይ አጭር ማስታወሻ ጻፉ፡፡ በማስታወሻችሁ ውስጥ ሥረሕዋን፣ ዝቀሕዋን፣ መካሕዋንና ሙቀ ሕዋን አጠቃሉ፡፡

**2.6 ዓለም አቀፋዊ የካርታ ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች(ውክሎች)**

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 5**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በካርታ ላይ የቅልመት አስፈላጊነትን ያስረዳሉ::
- በካርታ ላይ የዋሉትን ዋናዋና ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች ይለያሉ::
- በንድፍ ካርታ ላይ መረጃን ለማመልከት የታወቁ ምልክቶችና ወካይ ምልክቶችን ይጠቀማሉ፡፡
- ቀላል የካርታ መፍቻ ያዘጋጃሉ::

**ለ. ይዘቶች**

- በካርታዎች ላይ የቅልመቶች ጥቅም
- ዋናዋና ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

በመሬት ላይ የሚታዩ ገጽታዎችን በካርታው ላይ ለማመልከት የታወቁ ምልክቶችና ወካይ ምልክቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ እነዚህ በመሬት ላይ የሚታዩ ገጽታዎች ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሠራሽ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ካርታ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች በመሬት ላይ የሚስተዋሉ ገጽታዎችን ካርታ ላይ ለማሳየት ምልክቶችን እና ወካይ ምልክቶችን ወይም ቅልመቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ካርታ የራሱ ቋንቋ አለው፡፡ ቋንቋው በምልክቶችና በወካይ ምልክቶች ይገለጻል፡፡ የካርታ ወካይ ምልክት ምስል፣ ምልክት፣ ፊደል ወይም ምህፃረ ቃል ነው፡፡ እያንዳንዱ ምልክት በካርታ መፍቻ ላይ ይገለጻል፡፡ በካርታ ላይ ምልክቶች በመሬት ላይ የሚታዩትን ትክክለኛ ነገሮች ይወክላሉ፡፡ የሚወክሉት ነገር ግዝፈት በካርታው መስፈርት አማካይነት ይወሰናል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ -ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- ባለ 1:50,000 መስፈርት መልክዓ ምድራዊ ካርታ
- ንድፍ ካርታ

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- በወካይ ምልክቶች ላይ መረጃ ይሰብስቡ
- ወካይ ምልክቶችን የሚያሳዩ ካርታዎች ክፍል ውስጥ ዝግጁ ያድርጉ

- የተለያዩ ገጽታዎችን ለማመልከት ቅልመቶች የሠፈሩበት ካርታን በክፍል ውስጥ እንዲገኝ ያድርጉ።

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

***1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ

- ካርታ ምንድነው?
- ቅልመት ምንድነው?
- ምን ዓይነት ቅልመቶች በካርታ ላይ የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችን ያመለክታሉ?
- ወካይ ምልክቶች ምንድናቸው?
- ወካይ ምልክቶች በካርታ ላይ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

***2. የትምህርቱ አቀራረብ***

- 1፡50,000 መስፈርት ያለው ካርታ ይጠቀሙ
- በካርታ ላይ የቅልመቶች ጥቅምን ግለጹ
- ወካይ ምልክቶች ምን እንደሆኑ ተናገሩ
- ጥቅም ላይ የሚውሉ ልዩ ልዩ ወካይ ምልክቶችን አብራሩ
- በካርታዎች ላይ የሚሠፍረውን የካርታ መፍቻ ወይም መግለጫ ጽንሰ ሃሳብ ግለጹ።
- ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን በመልክዓ ምድር ካርታ ላይ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውን አድርጉ።
  - በመሬት ላይ ሰው ሠራሽ ወይም ተፈጥሮአዊ ገጽታዎችን በካርታ ላይ ለመወከል ጥቅም ላይ የሚውሉትን ቅልመቶች ለዩ
  - በካርታ ላይ የሠፈሩትን ወካይ ምልክቶችና የተወከሉበትን ገጽታ አስረዱ

### ረ. ምዘናና ክትትል

1. *ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

- ቅልመት ምንድንነው?
- ቅልመቶች በካርታ ላይ ለምን ጥቅም ላይ ይውላሉ?
- ወካይ ምልክቶችን ግለጹ
- ወካይ ምልክቶች ለምን በካርታ ላይ ጥቅም ላይ ይውላሉ?
- በካርታ ላይ ወካይ ምልክቶችን መጠቀም ምን ጥቀም አለው?
- የከፍታ ገጽታዎችን ለመግለጽ በካርታ ላይ የሚውሉትን የተለያዩ ቅልመቶች ጠቁሙ

*2. ክትትል*

ተማሪዎች፡-

- ቅልመቶችና ወካይ ምልክቶች ተጠቅመው የአካባቢአቸውን ንድፍ ካርታ እንዲስሉ ያድርጉ
- በካርታው ላይ ጥቅም ላይ የዋሉትን ቅልመቶችና ወካይ ምልክቶች በካርታው መፍቻ ወይም መግለጫ እንዲገልጹ ያድርጉ

## የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

### ሀ. እውነት ወይም ሀሰት

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

### ለ. ማዛመድ

6. መ
7. ሠ
8. ሀ
9. ሰ
10. ለ
11. ሐ

### ሐ. ምርጫ

12. ሐ
13. ለ
14. ለ
15. ሐ

### መ. ክፍት ቦታ ሙሉ

16. ቀይባሕር
17. ሥረ ሕዋ
18. 418 ሜትር
19. ሰባ በመቶ
20. 5600 ኪ.ሜ

### ሠ. አጫጭር መልሶች

1. ከባቢ አየር ማለት መሬትን እንደ ብርድልብስ የሸፈናት አየር ማለት ነው።
2. ዝቀ ሕዋ
3. በአንድ ቦታ ለረዥም ጊዜ በተከማቸ ውኃ አማካይነት ይፈጠራል።

# ምዕራፍ ሦስት

## አካባቢያችን

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-14**

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች***

***ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-***

- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ እፅዋት ሥርጭትንና የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን የሚቆጣጠሩ ምክንያቶችን መለየት ይችላሉ፡፡
- ሰዎች በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚያደርሷቸውን ተጽእኖዎች መንስኤዎችንና ውጤቶችን መረዳት ይችላሉ፡፡
- የብሔራዊ ፓርኮችን አስፈላጊነትና የእንክብካቤ ዘዴዎች ይገነዘባሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ላይ ጥፋት እንዳይደርስ የመከላከል ፍላጎትን ያዳብራሉ፡፡

***የምዕራፉ አደረጃጀት/ የምዕራፉ ዐበይት ይዘቶች***

- የምሥራቅ አፍሪካ እፅዋትና የዱር እንስሳት
- በምሥራቅ አፍሪካ የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር አንስሳትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎች
- የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነትና የአካባቢ ተፅእኖ፡፡
- አፈርና የውኃ ሀብትን የመጠበቅና የመንከባከብ ዘዴዎች
- የኢትዮጵያና የምሥራቅ አፍሪካ ብሔራዊ ፓርኮችና ጠቀሜታቸው

## 3.1፡ የምሥራቅ አፍሪካ እፅዋትና የዱር እንስሳት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- የዱር እንስሳት መገኘትን ከተፈጥሮ እፅዋት ስርጭት ጋር ያዛምዳሉ
- እንስሳት ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር ራሳቸውን እንደሚያለማምዱ ይገልፃሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንሰሳት ዓይነትና ስርጭት
- የዱር እንስሳት ከአካባቢያቸው ጋር ራሳቸውን አላምደው መኖራቸው፡፡

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

ምሥራቅ አፍሪካ ልዩ ልዩ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት አሉት፡፡ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ደኖችና የሣር ምድሮች ይገኛሉ፡፡ ደኖቹ የጠረፍ አካባቢ ደኖችንና የከፍተኛ ሥፍራ ደኖችን ያጠቃልላሉ፡፡ የጠረፍ አካባቢ ደኖች በአፍሪካ አኅጉር ምሥራቃዊ ዳርቻ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሥፍራ ሕንድ ውቅያኖስን ያዋስናል፡፡ በክልሉ የሚገኘው ሌላው የደን ዓይነት የከፍተኛ ሥፍራ ደን ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ደን ከምሥራቅ አፍሪካ ጋር ከምትዋሰነው በደቡብ ሱዳን፣ በኬንያ፣ በዩጋንዳና በሰሜናዊ ታንዛንያ ይገኛል፡፡ የከፍተኛ ሥፍራ ደን በተለያዩ ሥፍራዎች በሚገኙና ሃያ አምስት በሚሆኑ ራሳቸውን በቻሉ ደኖች የተጠናቀረ ነው፡፡ ሌሎች የእፅዋት ዓይነቶች የበረሃ፣ የሣር ምድርና የተራራማ አካባቢ ደንን ያጠቃልሉ፡፡

ከተለያዩ እፅዋት ጋር የተለያዩ ዓይነት የዱር እንስሳት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ እንስሳት ራሳቸውን አስማምተው የሚኖሩባቸው የተፈጥሮ አካባቢዎች የተራራማ ሥፍራ ደንን፣ የሳቫና ሣር ምድርን፣ የበረሃንና የበረሃ ነክ እፅዋት መገኛዎችን ያጠቃልላሉ፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### *1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የምሥራቃዊ አፍሪካ መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታዎች
- የእፅዋት ስርጭት ካርታዎች
- ንድፍ ካርታዎች

### *2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- ገለጻ
- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

### *3. ቅድመ ዝግጅት*

- ለተጨማሪ ንባብ የሚውሉ ጽሑፎችን መምረጥ
- በተቻለ መጠን በቂ መረጃ መሰብሰብ
- የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በክፍል ውስጥ ዝግጁ ማድረግ
- ተማሪዎችን በቡድን መከፋፈል
- ለተቋቋሙት ቡድኖች የሚያገለግሉ ንዑስ ርዕሶች መምረጥ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### *1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቅርቡ

- የተፈጥሮ እፅዋት ምንድናቸው?
- የተፈጥሮ እፅዋት ስርጭትን የሚወስኑ እውነታዎች ምንድን ናቸው?
- የዱር እንስሳት በአንድ ሥነምኅዳር ውስጥ ራሳቸውን የሚያቆራኙት ለምንድን ነው?
- ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ከተማሪ መጽሐፍ መጠቀም ይችላሉ፡፡

### *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- የምሥራቅ አፍሪካን  መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታዎች/ የእፀዋት ስርጭት ካርታዎችን በመጠቀም ተማሪዎች፡-

- በአፍሪካ ምሥራቃዊ ዳርቻ
- በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች
- ኬንያ፣ ዩጋንዳና ሶማሊያ በመሳሰሉ አገሮች የሚገኙ የእፅዋት ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ ጠይቁ
- ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸውና እያንዳንዱ ቡድን የደኖችን፣ የሣርምድርንና የበረሃነክ ሥፍራ እፅዋት ገጽታዎችን እንዲዘረዝር ያድርጉ
- በክልሉ የእፅዋት ዓይነቶች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጡ። ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ውስጥ የሚገኙትን እንስሳት በሣር በልና በሥጋ በል እንስሳት እንዲከፍሉአቸው ያድርጉ
- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡት የቡድንና የግል ሥራዎች መሥራታቸውን ያረጋግጡ። ከዚህ በኋላ የትምህርቱን ርዕስ ዋናዋና ሃሳቦች በማንሳት ትምህርቱን ያጠቃሉ።

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው።

- በሣር ምድር ምን ዓይነት እፅዋት ይገኛሉ?
- በበረሃ ነክ ሥፍራዎች በስፋት የሚገኙትን እፅዋት ዘርዝሩ
- በሚከተሉት ሥፍራዎች ምን ዓይነት እንስሳት ይገኛሉ?
    - በደኖች
    - በሣር ምድሮች
    - በበረሃ ነክ ሥፍራዎች

***2. ክትትል***

ተማሪዎቹን ከሚከተሉት በአንዱ ላይ አጭር ማስታወሻ እንዲጽፉ ንገሯቸው።

- የእፅዋት ዓይነቶች በኢትዮጵያ
- የሣር ምድር በኬንያ
- የተራራ ደኖች በዩጋንዳ

## 3.2. በምሥራቅ አፍሪካ የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን ስርጭት የሚወስኑ ሁኔታዎች

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡

- የተፈጥሮ እፅዋት ስርጭትን የሚወስኑትን ሁኔታዎች ይለያሉ::
- በሰው ልጅ ጫና መንስኤነት የተፈጥሮ አካባቢ ሲጎዳ የዱር እንስሳት ሕልውና እንደሚጎዳ ያስረዳሉ፡፡
- በምሥራቅ አፍሪካ ስለሚገኙ እፅዋትና የዱር እንስሳት ሥነ ውበታዊ እሴትን ያደንቃሉ፡፡
- ቱሪዝም ለዱር እንስሳትና ለተፈጥሮ አካባቢ መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የእፅዋትንና የዱር እንስሳትን ሥርጭት የሚወስኑ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ምክንያቶች
- የዱር እንስሳት፡- የዓለም ቅርስ

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

በሌሎች ሥፍራዎች እንደሚስተዋለው ሁሉ በምሥራቅ አፍሪካም የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ሥርጭት ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ከተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ውስጥ አፈር፣ አየር ንብረትና ከፍታ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ዓይነቶችን ይወስናሉ፡፡

ከሰው ሠራሽ ምክንያቶች ዋነኛው የሕዝብ ብዛት ነው፡፡ የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የደን ሽፋን ይቀንሳል፡፡ የደን ሽፋን መቀነስ ደግሞ የእንስሳት መጠለያን ስለሚጎዳ እንስሳት ለመሰደድ ይገደዳሉ፡፡ ስለዚህ በአንድ የተፈጥሮ አካባቢ በሰዎች፣ በእፅዋትና በዱር እንስሳት መካከል ቁርኝት

ይኖራል፡፡ በዚህም ምክንያት አንዱ በሌላው ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በአንዱ ላይ የሚከሰት ተጽእኖ ሌሎቹን ይጎዳል፡፡

የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ለአካባቢ መጠበቅና ውበት ከፍተኛ ጥቅም አላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት የአገር ውስጥንም ሆነ የውጭ አገር ጎብኝዎችን ይስባሉ፡፡ የውጭ አገር ጎብኝዎች በመምጣታቸው ለአገር የውጭ ምንዛሪ ያስገኛሉ፡፡ የአገር ጎብኝዎች በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ችግር ስለሚያስከትሉ ለጥንቃቄ ያመች ዘንድ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

1. ***የመርጃ መሣሪዎች ጥቆማ***
   - የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታዎች
   - የዱር እንስሳት ፎቶግራፎችና ሥዕሎች

2. ***የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች***
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ
   - ሪፖርት አጻጻፍ

3. ***ቅድመ ዝግጅት***
   - ተስማሚ ካርታዎች፣ ፎቶግራፎችና ሥዕሎች ለእይታ ማብቃት
   - በተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ስርጭት ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩት ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ሁኔታዎች ላይ ተጨ ማሪ መረጃ መሰብሰብ
   - አጫጭር ማስታዎሻዎች ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

1. ***ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

   ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያቅርቡ
   - እፅዋት እንዲያድጉ የሚያደርጉ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

- የተፈጥሮ እፅዋት አስፈላጊነትን አስረዱ
- የአየር ንብረት ለውጦችን የሚያመጣው ምንድነው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ተማሪዎችን በቡድን ይከፋፍሉና እያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን ሠርቶ ለክፍል ውይይት ያቅርቡ

- የተፈጥሮ ሁኔታዎች በተፈጥሮ እፅዋትና በዱር እንስሳት ሥርጭት ላይ እንዴት ተጽእኖ ያሳድራሉ?
- በተፈጥሮ እፅዋትና በዱር እንስሳት ሥርጭት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድረውን ሰው ሠራሽ ሁኔታን እንዴት መቆጣጠር እንችላለን? ከዚህ በኂላ የትምህርቱን ዋና ዋና ሃሳቦች ይከልሱ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

- የተፈጥሮ እፅዋትን ሥርጭት የሚወስኑ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሁኔታዎች ምንድናቸው?
- የእፅዋት ሽፋን ለአደጋ የሚጋለጠው መቼ ነው?
- የሰው ቁጥር መጨመር የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን እንዴት ይጎዳል?
- ጎሪላዎች በየትኞቹ የምሥራቅ  አፍሪካ አገሮች ውስጥ ይገኛሉ?
- የዓለምአቀፍ የዱር እንስሳት ጥበቃ ድርጅትን አስረዱ፡፡
- የዱር እንስሳት እንዴት በገቢ ምንጭነት ያገለግላሉ?

*2. ክትትል*

ተማሪዎች በሚከተለው ርዕስ ላይ አንድ ገጽ ተኩል የሚያህል አጭር ማስታወሻ እንዲጽፉ አድርጉ፡፡

- የአየር ንብረት ለውጦች፣ በአንድ ሥነምኅዳር ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ አስረዱ

## 3.3 የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነትና በአካባቢው ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 4**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የሰው ልጅ ተግባሮችን ይገመግማሉ።
- በተፈጥሮ እፅዋት ብክነት የሰው ልጅ ታላቅ ድርሻ እንዳለው ያስረዳሉ።

**ለ. ይዘቶች**

- የሰዎች በተፈጥሮ አካባቢ ጣልቃ ገብነት መንስኤዎችና ውጤቶች

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

በተፈጥሮአዊ አካባቢ የሰዎች ጣልቃ መግባት ለተፈጥሮ አካባቢው መመሳቀል ምክንያት ነው። የሰዎች ጣልቃ ገብነት በብዙ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ይሁንና ዋነኛው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ነው። የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ለእርሻና ለግጦሽ የሚውል ተጨማሪ መሬት ያስፈልጋል። ይህ ጥያቄ ካልተሟላ ሰዎች ወደ ጥብቅ አካባቢዎች በመግባት ለእርሻና ለግጦሽ የሚውል መሬት መያዛቸው የግድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ጣልቃገብነት ወደፊት ለደኖች መውደምና ለአካባቢው በግጦሽ መራቆት ምክንያት ይሆናል። ከዚህም በላይ ለተወሳሰቡ ችግሮች መከሰት በር ይከፍታል። ይህም ማለት ደኖች ሲወድሙ የአካባቢው አየር ንብረት ይዛባል። የአየር ንብረቱ መዛባት ድርቅ እንዲከሰት ያደርጋል። የድርቅ መከሰት ደግሞ የጸና ረሃብ ያስከትላል። ረሃብ ደግሞ ፍልሰትና ሞትን ያስከትላል።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- ሥዕሎች ወይም ፎቶግራፎች

### 2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ
- ሪፓርት

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ለተማሪዎች የቤት ሥራ መስጠት
- በክፍል ውስጥ ሥዕሎችና ፎቶግራፎች ለእይታ ማብቃት
- ለተማሪዎች የሚሆን አጭር ማስታወሻ ዝግጁ ማድረግ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋቅ

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡፡

- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በመሬት አጠቃቀም ላይ ምን ተጽእኖ ያሳድራል?
- ሰዎች በመኖሪያ አካባቢአቸው የተጠበቁ ወይም የተከለሉ አካባቢዎችን ሰብረው የሚገቡት ለምንድነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎችን በቡድን ክፈሏቸውና ለእያንዳንዱ ቡድን ለውይይት የሚሆን ርዕስ ይመድቡ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የተወያየበትን ለክፍሉ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡

- በተፈጥሮ ሀብቶች ከአግባብ ውጭ መጠቀም ላይ ተወያዩ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ለተፈጥሮ እፅዋት መውደም እንዴት ምክንያት ሊሆን ይችላል?

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ግምገማ

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ማንሳት ይችላሉ፡፡

- የአፈር መሸርሸር ምን ማለት ነው?
- የአፈር መሸርሸር መንስኤ ምንድነው?

* በአንድ ሥነምኅዳር የውኃ እጥረት ቢከሰት በአካባቢው ላይ ምን ተጽእኖ ይኖራል?

2. *ክትትል*

ተማሪዎች በአከባቢአቸው የሚገኙ እፅዋትን ይጎብኙና የሰዎች ጣልቃገብነት በእፅዋቱ ሽፋን ላይ ባሳደረው አዎንታዊ ተጽእኖና አሉታዊ ተጽእኖ ላይ መግለጫ እንዲሰጡ ያድርጉ።

## 3.4፡ አፈርና የውኃ ሀብትን የመጠበቅና የመንከባከብ ዘዴዎች

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

* የአፈር ሀብትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይገልጻሉ::
* ውኃን እንዴት ማጣራት እንደሚቻል ያስረዳሉ::
* የውኃ ሀብትን እንዴት መያዝና መጠቀም እንደሚቻል ያብራራሉ::

**ለ. ይዘቶች**

* የአፈር ሀብት አጠባበቅ ዘዴዎች
* የውኃ ሀብት አያያዝና አጠባበቅ

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

እንክብካቤ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና በአግባቡ መጠቀምን ያመለክታል። ውኃና አፈር በጣም ጠቃሚ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች በመሬት ላይ የሰውንና የሌሎች እንስሳትን ሕይወት ስለሚታደጉ ነው። እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶች ለመንከባከብ የሚያመቹ በርካታ ዘዴዎች አሉ። ዋንኞቹ ዘዴዎች ማድነን፣ ዳግም ማድነን፣ የደን እርሻ፣ እርከን፣ ከፍታን ጠብቆ ወደጎን ማረስ፣ ሰብሎችን ማፈራረቅ፣ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀምን መቀነስና በምትኩ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን መጠቀም ናቸው። ከዚህም በላይ በአንድ ሥነምኅዳር የሚገኘን ውኃ በአግባቡ መያዝና መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። የውኃ አጠቃቀምን በአንድ

ሥነ ምኅዳር ከፍ ለማድረግ ከሚወስዱት አስፈላጊ እርምጃዎች አንዱ ውኃ ማቆር ነው። ከዚህም በላይ ውኃ ሁልጊዜ በንጽሕና መያዝ አለበት።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- ፎቶግራፎችና ምስሎች
- ተዛማጅ ጽሑፎች
- በራሪ ወረቀቶች

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ
- ክርክር

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የንባብ ሥራ ይስጡ
- የመርጃ መሣሪያዎችን በክፍል ውስጥ ለእይታ ያብቁ
- ለተማሪዎቹ የሚሆኑ አጫጭር ማስታዎሻዎች ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡-

- እንክብካቤ ምን ማለት ነው?
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ለምን እንከባከባለን?
- የአየር ብክለቶች ምንድናቸው?
- ኩሬ ምንድነው?
- ምንጭ ምንድነው?

2. *የትምህርቱ አቀራረብ*

- ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸው፤ እያንዳንዱ ቡድን እንዲወያይባቸው የሚከተሉትን ርዕሶች ስጡ፡፡
  - የደን እርሻ ጠቃሚነት
  - ውኃን ለመንከባበከብ የሚጠቅሙ ዘዴዎች
  - አፈርን ለመንከባበከብ የሚጠቅሙ ዘዴዎች
- ተማሪዎች "የአፈርን ለምነት ለመጠበቅ ብዙ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ መጠቀም ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም"? በሚለው ላይ ይከራከሩ
- ፎቶግራፎች፣ ምስሎች በመጠቀም የትምህርት ርዕሱን መሠረታዊ ሃሳብ ያጠቃሉ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

1. *ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ

- ስለእርከን ማብራሪያ ስጡ
- ድነናንና ዳግም ድነናን አነፃጽሩ
- የሰብል ማፈራረቅ ጥቅሞችን ዘርዝሩ
- የአየር ብክለትን የሚያስከትለው ምንድነው?
- በኩሬና በምንጭ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

2. *ክትትል*

- ከፍታን ጠብቆ አግድም ስለማረስ ሥዕል ሠርታችሁ ይህ ለአፈር እንክብካቤ ስለመጥቀሙ በጽሑፍ አስረዱ
- የእርከን ሥዕል ሠርታችሁ የዚህን የአፈር እንክብካቤ ዘዴ ጠቀሜታ በጽሑፍ አቅርቡ
- የውኃ ማቆር ዘዴን በሥዕል አሳይታችሁ ስለጠቀሜታው አስረዱ

## 3.5. የኢትዮጵያና የምሥራቅ አፍሪካ ብሔራዊ ፓርኮችና ጠቀሜታቸው

**የክፍለ ጊዜ ብዛት:- 2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የብሔራዊ ፓርኮች ዓላማና ጥቅምን ይተነትናሉ
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮችን በካርታ ላይ ያመለክታሉ
- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ዋና ዋና ብሔራዊ ፓረኮችን ይለያሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮች
- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

ብሔራዊ ፓርኮች በአንድ አገር ውስጥ የተለዩ የሕዝብ የመሬት ይዞታዎች ወይም የውኃ አካላት ናቸው፡፡ ብሔራዊ ፓርኮች በመንግሥታት የሚከለሉት ሥነምኅዳሮችን፣ የእፅዋትንና የእንስሳትን ዝርያዎች፣ ውብ መልክዓ ምድርን፣ ሥነ ምኅድራዊ አቀማመጦችን ወይም ታሪካዊ አለበለዚያም የአርኪዮሎጂ አካባቢዎችን ለመጠበቅና ለመንከባበከብ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በርካታ ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ አካባቢዎች አሏት፡፡ እነዚህ የተፈጥሮ አካባቢዎች የቱሪስት መስህቦች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ ታዋቂ ብሔራዊ ፓርኮች የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን፣ አቢጃታ-ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክን፣ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክን፣ ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን፣ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክን፣ ማጎ ብሔራዊ ፓርክን፣ ነጭሳር ብሔራዊ ፓርክን፣ ኦሞ ብሔራዊ ፓርክንና ያንጉዲ ራሳ ብሔራዊ ፓርክን ያጠቃልላሉ፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች ደግሞ የናይሮቢ ወላጆች የተለዩአቸው ግልገሎች መጠበቂያ ብሔራዊ ፓርክ፣ የታንዛንያ ሰረንጌቲ ብሔራዊ ፓርክ፣ ሳቮ ብሔራዊ ፓርክ በኬንያና ካባሌጋ ብሔራዊ ፓርክ

በዩጋንዳ ናቸው፡፡ ብሔራዊ ፓርኮች የእንስሳትና የእፅዋት ዝርያዎችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ አስፈላጊ ናቸው፡፡ አገር ጎብኝዎችን ይስባሉ፡፡ ከዚህም በላይ እንደቅርስም ያገለግላሉ፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊና ፖለቲካዊ ካርታዎች
- ፎቶግራፎችና ሥዕሎች
- ንድፍ ካርታዎች

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*

- ገለጻ
- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የንባብ ሥራ ስጧቸው
- የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በክፍል ውስጥ ለእይታ ያቅርቡ
- ለተማሪዎች የሚሆኑ አጫጭር ማስታዎሻዎች ያዘጋጁ

***ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት***

***1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ፡፡

- ብሔራዊ ፓርኮች ምንድናቸው?
- የብሔራዊ ፓርኮች ጥቅም ምንድነው?
- ጥብቅ አካባቢዎች ምንድናቸው?
- ጥብቅ አካባቢዎችና ብሔራዊ ፓርኮች በምን ይለያሉ?
- የአደን ሥፍራዎችን አብራሩ

***2. የትምህርት አቀራረብ***

ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸው፡፡ የሚከተሉትን የትምህርት ርዕሶች ለእያንዳንዱ ቡድን ይስጡ፡፡

- በኢትዮጵያ የብሔራዊ ፓርኮችን ጠቀሜታ አብራሩ
- ብሔራዊ ፓርኮችንና ጥብቅ አካባቢዎችን አነፃጽሩ
- ለትምህርቱ የተጠቆሙትን የትምህርት መሣሪያዎች በመጠቀም ትምህርቱን ያጠቃሉ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- ብሔራዊ ፓርኮች ለአካባቢው የሚሰጡት ጥቅም ምንድነው?
- ለአንድ አገር ወይም ክልል የብሔራዊ ፓርኮች ፋይዳ ምንድነው?

*2. ክትትል*

ተማሪዎች የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ አድርጉ

- የምሥራቅ አፍሪካን ንድፍ ካርታ በመሥራት ታዋቂ ብሔራዊ ፓርኮችን አመልክቱ
- የኢትዮጵያ ንድፍ ካርታ በመሥራት ብሔራዊ ፓርኮችንና ጥብቅ አካባቢዎችን አሳዩ፡፡

## የምዕራፍ ሦስት ክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

**ሀ. እውነት/ሐሰት**

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት

**ለ. ማዛመድ**

5. ለ    6. ረ    7. ሠ    8. ሰ    9. ሐ

**ሐ. የምርጫ ጥያቄዎች**

10. ሐ
11. ለ
12. ሀ
13. ሀ
14. መ
15. ሐ

**መ. ክፍት ቦታ መሙላት**

16. የአየር ንብረት፣ ከፍታና የአፈር ዓይነት
17. የሰው ልጅ
18. ዓለም አቀፍ የዱር እንስሳት ጥበቃ ድርጅት
19. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት
20. ድነና

**ሠ. አጫጭር መልሶች**

1. አካባቢን ሥነምኅዳር ለመጠበቅና ገቢ ለማስገኘት።
2. አቢጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣ የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ወዘተ ...የባቢሌ ዝሆን መጠበቂያና መከለያ፣ ሰንቀሌ የቆርኬ መጠበቂያና መለኪያ፣ ያቤሎ መጠበቂያና መለኪያ ወዘተ...
3. አካባቢያቸውን በንጽህና በመያዝ ነው።
4. የማገዶ እንጨት ለማግኘት ዛፎችን መቁረጥ፣ የእርሻ ሥፍራ ለማግኘት ደንን አላግባብ መመንጠር፣ ሕገወጥ አደን

# ምዕራፍ አራት

## ሕዝባዊ ጉዳዮች

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 16**

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-***

***ተማሪዎች የምዕራፉን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ***

- ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡
- ለሕፃናት መብቶች ጥሰትና መከላከያ መንገዶችን በምሣሌዎች መስጠት ይችላሉ፡፡
- ግዴታዎቻቸውን ወይም ኃላፊነቶቻቸውን ይገነዘባሉ፡፡
- የምሥራቅ አፍሪካ አጋር መንግሥታትን፣ አባል አገሮችን የጋራ ዓላማዎች ይለያሉ፡፡

***የምዕራፉ አደረጃጀት/ የምዕራፉ ዐበይት ይዘቶች***

- የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት
- የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት
- የሕፃናት መብቶችን ማስከበሪያ ስልቶች
- ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባሮችና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች
- የአጋርነት ጉዳዮች

**4.1፡- የሥነሕዝብ ጉዳዮች**

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 3***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ኤችአይቪ/ኤድስን በመከላከል ረገድ የኅብረተሰብ ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገልጻሉ

- ኤችአይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ከሚኖር ወገኖችና ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዴት መማርና መኖር እንደሚቻል አዎንታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ያሳያሉ፡፡
- ኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖችን ከማግለልና ከማዳላት ይልቅ በምትኩ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳትና አብሮ ለመኖር ኃላፊነት ይወስዳሉ

**ለ. ይዘቶች**

- በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎና በዜግነት ኃላፊነት ኤች አይቪ/ኤድስን መከላከል
- ማግለልና መድሎን ማቆም
- ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ላለ ወገኖች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ሁለት ዋና ዋና የሕዝብ ችግሮች ተጋርጠውባቸዋል፡፡ አንዱ የኤች አይቪ/ኤድስ መስፋፋት ነው፡፡ ይህ በሽታ በክልሉ የሞት አደጋ ከሚያስከትሉት በሽታዎች አንዱ ነው፡፡ በሽታው አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠቃው አምራቹን የኅብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ የተማሩና ባለሙያ ሰዎችን ይገድላል፡፡ የቤተሰብ ተቋምን ያፈርሳል፡፡ ይህ ሁኔታ በክልሉ ላይ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ችግሮች ያስከትላል፡፡

**መ. የትምህረት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴ**

1. ***የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***
   - የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊ ካርታ
   - ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የተገናዘበ ፖስተር
2. ***የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች ጥቆማ***
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ
   - ምልከታ
   - ሪፖርት መጻፍ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የንባብ ሥራ ስጡ
- የማስተማሪያ መሣሪያዎች ክፍል ውስጥ እንዲገኙ ያድርጉ
- ለተማሪዎች የሚሆኑ አጫጭር ማስታወሻዎች ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ

- ኤች አይቪ/ኤድስ ምንድነው?
- በኤች አይቪ እና በኤድስ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት መንስኤዎች ምንድናቸው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ክፍልዎን በትናንሽ ቡድኖች ይከፋፍሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲሠራ ያድርጉ፡፡ ቡድኑ የውይይት ግኝቱን ለክፍሉ በዘገባ መልክ እንዲያቀርብ ያበረታቱ፡፡

- ኤች አይቪ/ኤድስ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ እንዴት ይተላለፋል?
- ራሳችሁን ከኤች አይቪ/ኤድስ እንዴት ትከላከላላችሁ?
- ኤች አይቪ/ኤድስ በማኅበረሰብ ላይ ምን ዓይነት ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ችግሮች ያስከትላል
- የ'መ' ሕግጋት ምንድናቸው?
- ኤች አይቪ/ኤድስ የማይተላለፍባቸው ጥቂት መንገዶች ምንድናቸው?
- ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችንና ቤተሰቦቻቸውን እንዴት እናስተናግዳለን?
- በመጨረሻም የትምህርቱን ዋናዋና ነጥቦች ያጠቃሉ፡፡ ማጠቃለያውን ለመስጠት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ጥቆማን ተጠቀሙ

ረ. ምዘናና ክትትል

1. *ግምገማ*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላሉ፡፡

- በምን ዓይነት ሁኔታዎች ነው ኤችአይቪ/ኤድስ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚተላለፈው?
- የ'መ' ሕግጋት ምንድናቸው?

2. *ክትትል*

- የ'መ' ሕግጋትን የሚገልጽ ቻርት ስሩ
- የኤች አይቪ/ኤድስን ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግለጹ

## 4.2፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 3***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የልማት ብቃት ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የሕዝብ ብዛት ዕድገት በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያለውን ተጽእኖ ከምሥራቅ አፍሪካ አንፃር ይተነትናሉ፣
- የሕዝብ ብዛት እድገት በኀበራዊ አካባቢ ላይ ያለውን ተጽእኖ ከምሥራቅ አፍሪካ አንፃር ይተነትናሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች፡-**

- የተፈጥሮ እፅዋት በመጨፍጨፍ፣ድርቅ፣ረሃብ፣የእርሻ መሬት እጥረትና መበጣጠስ የሚያስከትሉት ችግር፣
- የምግብና መጠለያ እጥረት፣አለመረጋጋትና የአካባቢ መበከል፣

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ፡-**

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለሕይወት በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ የፍላጐቶች መጨመር እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ በክልሉ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ለምግብ እጥረት መከሰት መንስኤ ይሆናል፡፡ የምግብ እጥረት ደግሞ ረሃብና ስውር ረሃብን ያስከትላል፡፡ ለማገዶና

ለግንባታ ሲባል እፅዋት ስለሚጨፈጨፉ ድርቅ፣ ረሃብና የአየር ንብረት ለውጥ ይከሰታሉ። የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር በገጠሪቱ ኢትዮጲያም ሆነ በምሥራቅ አፍሪካ የእርሻ መሬት ፍላጐት ስለሚጨምር የመሬት እጥረትና መበጣጠስ ይከሰታል። የመጠለያ እጥረት፣አለመረጋጋትና የአካባቢ መበከልም ይስተዋላል። በአጠቃላይ በተፈጥሮ አካባቢው ላይ ከፍተኛ ጫና ያስከትላል።

**መ. የትምህርት መረጃ መሣሪያና የመስተማሪያ ሥነ-ዘዴ፡-**

*1. የመረጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የሕዝብ ብዛት መረጃዎችን የሚያሳይ ቻርት
- የተበጣጠሱ የእርሻ ሥፍራዎችን የሚያሳይ ፎቶግራፍ
- በስውር ረሃብ መንስኤነት የተጎዱ ሕፃናትን የሚያሳይ ፎቶግራፍ

*2. የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች ጥቆማ*

- ገላጻ
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ
- ውይይት

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የንባብ ቅድመ ዝግጅት ይስጡ
- የማስተማሪያ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ እንዲገኙ ያድርጉ
- ለተማሪዎች የሚሆኑ አጫጭር ማስታወሻዎች ያዘጋጁ
- ለትምህርቱ ርዕስ ተስማሚ የሆኑ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች ይመረጡ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት፡-**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ።

- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምን ማለት ነው?
- የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ምን ምን ችግሮች ይከሰታሉ?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ፡-*

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምን ማለት እንደሆን በምሳሌ ደግፈው ያብራሩ። በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን ይዘርዝሩ። ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በቡድን ከፋፍለው በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ።

- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በምግብ አቅርቦት ላይ ምን ተጽእኖ ያሳድራል?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር ለመኖሪያ ቤት እጥረት እንዴት ምክንያት ይሆናል?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከረሃብና ከስውር ረሃብ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
- በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት ለምን የእርሻ ሥፈራዎች ይበጣጠሳሉ?

**ረ. ምዘናና ክትትል፡-**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው፡-

- የሕዝብ ቁጥር በምን በምን ምክንያት ይጨምራል?
- የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ምን ምን ችግሮች ይከሰታሉ?
- የሕዝብ ቁጥር እድገት እንዴት በአካባቢ ላይ ብክለት ያስከትላል?

*2. ክትትል*

- በ1976፣1982፣1986፣1995፡1999 እና 2000 ዓ.ም የነበረውን የኢትዮጲያ ሕዝብ ቁጥር የሚያሳይ ግራፍ ሥሩ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ለአፈር መሸርሸር እንዴት መንስኤ ይሆናል?

**ንዑስ ርዕስ 4.3፡ የሕፃናት መብቶችና አያያዝ**

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 3***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- ስለ መሠረታዊ የሕፃናት መብቶች ምንነት ይገልፃሉ
- በኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች ጥሰት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ያስረዳሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች መሠረተ ሃሳብ
- የሕፃናት መብት መጠበቀና መከበር
- በተባበሩት መንግሥታት ድርድት የወጡ የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች
- የሕፃናት መብት ጥሰት መንሥኤዎች

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

የአሁኑ ሕፃናት የነገ አገር ገንቢ ዜጎች ናቸው፡፡ ይሁንና ይህን ለማድረግ በበቂ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ሕፃናትን ለቁምነገር ለማብቃት መሠረታዊ መብቶቻቸው መጠበቅ አለባቸው፡፡ ሕፃናት እንደ ግለሰብ ማንኛውም ዜጋ ያሉትን መብቶች ይጋራሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደሕፃንነታቸው ልዩ መብቶች አሏቸው፡፡ በኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች በአገሪቱ ሕገመንግሥት ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ እ.ኤ.አ የ1997ቱ የፌደራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 የሕፃናት መሠረታዊ መብቶችን ያወሳል፡፡ ለሕፃናት መብቶች መከበር የቆሙ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች አሉ፡፡ በጣም የታወቁት የተባበሩት መንግሥታት፣ ዩኔስኮ እና ዩኒሴፍ ናቸው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. መርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*

- የ1987 የኢትዮጵያ ፌደራል ሕገመንግሥት
- የተባበሩት መንግስታት የሕፃን መብቶች አዋጅ ግልባጭ

*2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች ጥቆማ*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የንባብ ሥራ ይስጧቸው
- የሚከተሉትን ዝግጁ ያድርጉ፡-
  - ሕገ መንግሥት
  - ፎቶግራፎች እና ሥዕሎች፡፡ እነዚህ ለክፍል ውይይት ያገለግላሉ፡፡
  - አጭር ማስታወሻ አዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያቅርቡ፡፡

- የሕፃናት መሠረታዊ መብቶች ምንድናቸው?
- ለሕፃናት መብቶች የቆሙ ታዋቂ ድርጅቶችን ስያሜ ጥቀሱ?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ክፍልዎን በትናንሽ ቡድኖች መከፋፈል ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ለውይይት ያመች ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲሠራ ያድርጉ፡፡

- የአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ልዩ ጥንቃቄ የሚፈልጉት ለምንድነው?
- ኅብረተሰቦች ለሕፃናት እድገትና ትምህርት ልዩ ትኩረት የሚሰጡት ለምንድነው?

**ረ. ምዘናና ክትትል**

1. *ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቁ

- የሕፃናት መሠረታዊ መብቶች ምንድናቸው?
- መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስለመከበራቸው በምን ያረጋግጣሉ?
- ለሕፃናት መብቶች የቆሙ ድርጅቶችን ዘርዝሩ

*2. ክትትል*

ተማሪዎች ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ አድርጉ

- በሕፃናት መብት ላይ በተባበሩት መንግሥትት ድርጅት የወጡ ስምምነቶችን ዘርዝሩ
- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገራት ከምን ተነስተው ነው የሕፃናት መብትን በተመለከተ በሕገ መንግሥታቸው ውስጥ ያካተቱት?

**4.4፡- የሕፃናት መብቶችን ማስከበሪያ ስልቶች**

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡-2***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የሕፃናት መብቶችን ለማስከበር የሚረዱ መንገዶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ
- የእኩያ ግፊትን ይቋቋማሉ

**ለ. ይዘቶች**

- የመብት ጥሰት ምንነት
- የሕፃናት መብት ጥሰት መንሥኤዎች
- ግዴታንና ኃላፊነትን መወጣት

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

በተለያዩ ሀገራት ወይም አካባቢዎች በበርካታ ምክንያቶች የሕፃናት መብት ጥሰት ይፈጸማል፡፡ የመብት ጥሰቶች በአካላዊ ጉዳት፣በሥነ-ልቡና መሰበር፣በስሜት ጉዳትና በቅጣት ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ በሕፃናት ላይ የሚደርስን የመብት ጥሰት ለማስወገድ ዜጎች ሁሉ ንቁ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የሕፃናትን መብት ጥሰት ለመከላከል በመብት ጥሰት ላይ ዜጎች ሁሉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከአደጋም እንዴት ማምለጥ እንደሚቻል ማሳወቅና ተግባራዊነቱንም መከታተል ተገቢ ነው፡፡

ሕፃናት ራሳቸውን ከጥቃት ለማዳንና ከአደጋ ለማምለጥ የሚያስሏቸውን ክህሎት ማዳበር አለባቸው፡፡ ከመብት ጥሰቶች ለማምለጥ የመጀመሪያው ዘዴ ዘውትር ንቁ በመሆን አካባቢን ማስተዋል ነው፡፡ በምጣኔ ሀብት እድገት ኋላ ቀር መሆን በቤተሰቦችና በማኅበረሰብ ላይ ጫና ያስከትላል፡፡በዚህም ምክንያት ሕፃናት ከባድ የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ፡፡ ገንዘብ ለመበደር ሕፃናት በመያዣነት ለአበዳሪ ይሰጣሉ፡፡ ሕፃናት የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ በገንዘብ ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋሉ፡፡ በልመና እንዲሠማሩ ይደረጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ትምህርታቸው ይቋረጣል፡፡ በወሲብ ንግድ ላይ ተሠማርተው ገንዘብ እንዲያመጡ ይደረጋሉ፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትና በኋለ ቀር አስተሳሰብ ምክንያት በሕፃናት ላይ ከባድ አካላዊ ቅጣት፣ያለዕድሜ ጋብቻ የአካል ጉዳትና የመንፈስ ስብራት ይደርሳል፡፡ስለዚህ በምጣኔ ሀብት እድገት ኋላቀርነትና የማኅበራዊ እድገት አናሳነት ለሕፃናት መብት ጥሰት ዋና ምክንያቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡
ሕፃናት እንደማንኛውም ሰው መብት እንዳላቸው ሁሉ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ

1. ***የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***
   - በጣፋጭ ምግቦች፣ በመጫዎቻ ዕቃዎች በገንዘብ ሕፃናትን የማታለሉ ተግባራት ሲፈጸሙ የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች
   - ከባድ አካላዊ ቅጣት የሚያሳይ ፖስተር
   - የትምህርት ቤት ደንብ
2. ***የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች ጥቆማ***
   - ገለጻ
   - ውይይት
   - ምልከታ
   - ጥያቄና መልስ

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- የንባብ ሥራ ይሰጧቸው
- የሚከተሉትን ዝግጁ ያድርጉ
  - በመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ሥር የተዘረዘሩትን ዝግጁ ያድርጉ
  - አጭር ማስታወሻ አዘጋጁ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት፡-

### 1. ትምህርቱን ማስተዋዎቅ

ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያዎች ያቅርቡ

- በሀገራችን በሕፃናት ላይ የሚደርሱ የሕፃናት መብት ጥሰቶችን የመከላከለና የማስቆም ኃላፊነት የማን ነው?
- የሕፃናት መብት የሚገስሱባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

የክፍልዎን ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ከፋፍሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉትን እንዲሠራ ያድርጉ፡፡

- የሕፃናት መብቶችን የሚጠብቁ በርካታ ድርጅቶች ቢኖሩም የሕፃናት መብቶች ጥሰት መቆም አልቻለም፡፡ ለምን?
- የሕፃናት መብቶች በሚጥሱ ጎጂ ልማዳዊ ተሞክሮዎች ላይ አጭር ማስታወሻ ጻፉ

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ግምገማ፡-

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ጠይቁ

- የአቻ ግፊት ምንድነው? ምሳሌ በመስጠት አስረዱ
- ግዴታንና ኃላፊነትን መወጣት ምን ጥቅም አለው?
- የሕፃናት መብት ጥሰት መንስኤዎችን ዘርዝሩ

*2. ክትትል፡-*

ተማሪዎች የሚከተሉትን እንዲሠሩ ያድርጉ፡-

- የሕፃናት መብቶችን የሚጥሱ ፎቶግራፎች ወይም ስዕሎች በመሰብሰብ ማብሪሪያ ስጡ
- ከመብት ጥሰት ለማምለጥ መውሰድ ያለባችሁን እርምጃዎች ዘርዝሩ
- ያለዕድሜ ጋብቻ በሚያስከትለው ጉዳት ላይ ተወያዩ
- የመብትና የግዴታን ልዩነትና አንድነት አስረዱ

**4.5. ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባራትና መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋሚ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ድንገተኛ አደጋዎችን እንዴት እንደሚያስወግዱ ይገልጻሉ
- ድንገተኛ አደጋዎች ቢያጋጥሟቸው እንዴት እርምጃ እንደሚወስዱ ያስረዳሉ

**ለ. ይዘቶች**

አደጋ የሚያስከትሉ ተግባራትና የደኅንነት እርምጃ አወሳሰድ

- ኮረንቲ
- መርዝ
- እሳት
- ፈንዲዎች

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ**

በአሁኑ ዘመን ሰዎች በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቀማሉ፡፡ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በጥንቃቄ ካልተያዙ አደገኞች ናቸው፡፡ በሕይወትም ሆነ በንብረት ላይ አደጋ እንዳይከተል በእነዚህ ነገሮች በጥንቃቄ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ኮረንቲ፣መርዝንና ፈንጂዎችን ያጠቃልላሉ፡፡

እሳት በተፈጥሮ የሚገኝ ሲሆን ብርሃን፣ሙቀትና ጉልበት ለመስጠት ጠቃሚ ነው።ይሁን እንጂ በጥንቃቄ ካልተያዘ ቃጠሎ ሊያስከትል ይችላል። ሁሉም ብረት ነክ ነገሮችና እርጥብ ነገሮች የኮረንቲ ፍሰትን ያስተላልፋሉ። ስለዚህ የኮረንቲ ፍሰት የሚያስተላልፉ የኘላትቲክ ሽፋን የሌላቸውን ሽቦዎች መንካት፣ ሽቦዎችን በእጅ ማገናኘት፣ በእርጥብ እንጨት የተላጡ የኮረንቲ ሽቦዎችን መንካት ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል።

መርዝ አደገኛ የሆነ ሰው ሠራሽ ነገር ነው። በተፈጥሮም መርዛማ ነገሮች ሊገኙ ይችላሉ። ብዙ መርዞች የሚፈበረኩት በኢንዱስትሪዎች ነው።መርዞች ኬሚካሎችም ሆነው በጠጣር፣በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ ይገኛሉ። መርዝ ከተዋጠ ወይም ከሰውነት ጋር ከተዋሐደ ጉዳት ወይም ሞት ያስከትላል።

ፈንጂዎች በአብዛኛው በጦር አውድ የሚውሉ ሰው ሠራሽ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ናቸው።ጦርነቶች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች አደጋ ለመጣል ፈንጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። እንዲህ ያሉ ፈንጂዎችን ከመንካት መቆጠብ ለደህንነት በጣም ጠቃሚ ነው።

እሳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም በአጠቃቀም ላይ በሚፈጠር ስህተት አደገኛ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እሳት ሲያያዝ በአካባቢው ተቀጣጣይ ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ**

***1. የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ***

- የኤሌክትሪክ ሽቦ
  - በኘላስቲክ የተሸፈነ
  - የኘላስቲክ ሽፋን የሌለው
- የፈንጂ ነገሮች ምስል
  - ክብሪት
  - ፍሊት
  - ዲቶል

*2. የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች*

- ውይይት - ጥያቄና መልስ
- ገላጻ - ምስከታ

*3. ቅድመ ዝግጅት፡-*

- ለተማሪዎች የሚሆን የንባብ ሥራ አዘጋጁ
- በመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ሥር የተዘረዘሩትን ዝግጁ ያድርጉ
- ለተማሪዎች በአደገኛ ነገሮች ላይ እንዲወያዩ የሚያደርጓቸው ጥያቄዎች ያዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት**

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላሉ?

- ኮረንቲ ምንድንነው? ምን ምን አገልግሎት ይሰጣል?
- በኮረንቲ ሽቦ ስንጠቀም ለምን መጠንቀቅ ያስፈልገናል?
- ፈንጂ ምንድነው? የፈንጂ አደጋ እንዳይደርስ ምን ምን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል?
- በአካባቢያችን ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገር ግን መርዝነት ያላቸው ነገሮችን ዘርዝሩ
- እሳት ጠቃሚ መሆኑን ታውቃላችሁ። አደገኛ የሚሆነው መቼ ነው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸው። እያንዳንዱ ቡድን በሚከተሉት ላይ እንዲወያይ አድርጉ።

- ለአደጋ የሚያጋልጡ ነገሮች ምን፣ምንድናቸው?
- አደጋ ከሚያመጡ ነገሮች ለመጠንቀቅ ምን ምን ማድረግ አለባችሁ?

- በተፈጥሮ መርዛማ የሆኑ ነገሮች ከምን ከምን ይገኛሉ?መልስ ከመስጠታችሁ በፊት ሰዎች በመጠየቅ መረጃ አግኙ

## ረ. ምዘናና ክትትል

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን መጽሐፍት በማንበብ አደጋ በሚያመጡ ነገሮች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ

- እርጥብ ነገሮች በመያዝ የተላጠ የኮረንቲ ሽቦ ሲነካ ለምን አደገኛ ይሆናል?
- ከፈንጂ አደጋ ራስን ለመታደግ ምን መደረግ አለበት?
- እሳት ባለበት ሌሎች ተቀጣጣይ ነገሮችን እንድናስወግድ የምንጠየቀው ለምንድነው?

*2. ክትትል*

- ተማሪዎችን በኮረንቲ ጥቅምና አደጋ አምጪነት ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ
- መርዝነክ የሆኑ ነገሮች ጥቅም ላይ ሲውሉ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ እንዲዘረዝሩ ተማሪዎችን ጠይቋዋው
- ተማሪዎችን በእሳት አጠቃቀምና አገልግሎት ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ጠይቋቸው፡፡

## 4.6፡- የአጋርነት ጉዳዮች

***የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 3***

## ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኘውን ክልላዊ ድርጅት በስም ይጠራሉ
- የእያንዳንዱን ክልላዊ ድርጅት ተግባር ይገልጻሉ
- የምሥራቅ አፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች የሚያካልሏቸውን ሥፍራዎች ይጠቁማሉ
- የትብብር ግቦች አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፡፡

ለ. ይዘቶች

- የክፍለ አኅጉራዊ ድርጅቶች
- መልክዓምድራዊ ሽፋን
- የአጋርነት ዓላማዎች

ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሳብ

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች በርካታ ችግሮችን ይጋራሉ፡፡ ዋናዎቹ በረሃማነት፣ አለመረጋጋት፣ ድህነትና የተወሰኑ የጋራ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠቀም ያለው ኢፍትሃዊነት ናቸው፡፡ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ማግኘት ከእያንዳንዱ ሀገር አቅም በላይ ነው፡፡ ችግሮቹን ለመፍታት ችግሮቹን የሚጋሩ ሀገሮችን የጋራ ጥረት ይፈልጋል፡፡ አንዱ የትብብር አቅጣጫ ክፍለ አኅጉራዊ ድርጅቶች ማቋቋም ነው፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ ብዙ ክፍለ አኅጉራዊ ድርጅቶች አሉ፡፡ በጣም የታወቁት ኢጋድና የናይል ተፋሰስ ድርጅት ናቸው፡፡ የሁለቱ ድርጅቶች ጂኦግራፊያዊ ሽፋን የተለያየ ነው፡፡ ኢጋድ ስድስት ሀገሮች ይይዛል፡፡ የናይል ተፋሳስ የምሥራቅ አፍሪካን አስራአንድ ሀገሮች ያጠቃልላል፡፡ ድርጅቶቹ የተለያዩ የትብብር ግቦች አሏቸው፡፡ የናይል ተፋሰስ በናይል ውኃ ፍትሃዊ ክፍፍልና በእኩልነት መጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ ኢጋድ በልማት ሰፊ ሥራዎች ላይ የሚያተኩር ድርጅት ነው፡፡

መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ- ዘዴ

1. *የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ*
   - የአፍሪካ ፓለቲካዊ ካርታ
   - የአፍሪካ መልክዓ ምድራዊ ካርታ
   - ፎቶግራፎችና ሥዕሎች

2. *የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች*
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ
   - ምልከታ

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- የንባብ ሥራ አዘጋጁ
- የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በክፍል ውስጥ ያስቀምጡ
- ለክፍል ውይይት የሚያገለግሉ ጥያቄዎች ይምረጡ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- የምሥራቅ አፍሪካን ጥቂት ክፍለ አኅጉራዊ ድርጅቶች ጠቁሙ
- የናይል ተፋሰስ ሀገሮችን ዘርዝሩ

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሏቸው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ እንዲወያይ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን ግኝቱን ለክፍሉ ያቅርብ፡፡

- የትብብር ግብ ምንድነው?
- የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ምን ምን የጋራ ሀብቶችና ችግሮች በጋራ ይካፈላሉ፡፡
- ከቡድን ውይይት በኋላ የትምህርቱን መሠረታዊ ነጥቦች በማንሳት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ግምገማ

ተማሪዎች የአፍሪካን ፓለቲካዊ ካርታ ተጠቅመው፡-

- የኢጋድንና የናይል ተፋሰስ አባል አገሮችን እንዲያሳዩ፣
- የኢጋድና የናይል ተፋሰስ ሽፋንን እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

### 2. ክትትል

ተማሪዎችን በክፍለ-አኅጉራዊ ድርጅቶች ጠቀሜታዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

## የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

**ሀ. እውነት/ሐሰት**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት

**ለ. ማዛመድ**

5. ሠ  6. መ  7. ረ  8. ረ

**ሐ. የምርጫ ጥያቄዎች**

9. ለ  10. ሀ  11. መ

**መ. አጫጭር መልሶች**

12. ሕገ ወጥ የሕፃናት ዝውውር የተከለከለ መሆኑ
    - ሕፃናት ከጉልበት ብዝበዛ ነፃ መሆናቸው
    - ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሠማራት የተከለከለ መሆኑን
13. ዝቅተኛ የምጣኔ ሀብት መኖርና የማኅበራዊ እድገት ኋላ ቀርነት
14. - የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት
    - የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ

## ዋቢ መጻሕፍት


- B.A ogot and S.A kielan (eds) zamani: A survey of East African History Nairobi: EAPH long mass of Kenya, 1968).
- Bahru Zewde, Richard Pankhurst and Taddese Beyene (eds), proceedurings of the Eleventh futernational conference of Ethiopian Studies, Vol II, IES, A.A.W, 1994
- Robert J. Lowaherz, Population (Mankato: Creative Eductina press, 1970).
- Roy T. Matthews and F. Dewitt platt, the Western Humanitier, 5th Edition (New York: Mc Graw-Hill, 2004)
- Sir Kenneth Blaxter, people, food and Resources (Cambridge: Cambridge university press, 1986).